Desciple Bible University

# ስነ ስብከት

# (Homiletics)

## ኮርስ ኮድ Ho-58

*ይህንን ማስተማሪያ ሞጁል ያለ ዩኒቨርሲቲዩ ፈቃድ*

*ማባዛት በህግ የተከለከለ ነው።*

*© Copy Right Disciple Bible University 2013*

*All Rights Reserved*

**ሌሎች ኮርሶችን መማር ከፈለጉ**

- ኢ-ሜይል፦ *registrardbu*@gmail.com
- ስልክ፦ +251978011117 / +251975156595
- ድረገጽ፦ www.disciplebibleuniversity.com
- ኢ-ሌርኒንግ፦ www.disciplebibleuniversity.org
- ፌስቡክ፦ Disciple Bible University
- ቴሌግራም፦ @disciplebibleuniversity

# ማውጫ


መግቢያ .......... 4

ምዕራፍ 1 ስብከት እና ሰባኪ .......... 5

1.1 የስብከት አስፈላጊነት .......... 5

1.2 የአሰባበክ ስልት .......... 6

1.3 ስብከትና ትምህርት .......... 8

1.4 የሰባኪ ማንነት .......... 10

መልመጃ ጥያቄ አንድ .......... 13

ምዕራፍ 2 የስብከት ዓይነቶች .......... 14

2.1 ርዕሳዊ ስብከት .......... 14

2.2 አውደ ምንባባዊ ስብከት .......... 17

2.3 ገላጭ ስብከት .......... 21

መልመጃ ጥያቄ ሁለት .......... 24

ምዕራፍ 3 የስብከት ዝግጅት እና አቀራረብ .......... 25

3.1 የስብከት ዝግጅት .......... 25

3.2 የስብከት አቀራረብ .......... 31

መልመጃ ጥያቄ ሶስት .......... 33

ምዕራፍ ስኬታማ ስብከት .......... 34

4.1 የዓይነተኛ ስብከት መለያዎች .......... 34

4.2 የስብከት ተግዳሮቶች .......... 40

መልመጃ ጥያቄ አራት .......... 44

ዋቢ መጽሐፍት .......... 45

# መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልዕክት ለማስተላለፍ የስብከት መርህ የተከተለ ስልታዊ ትምህርት በጣም አስፈላጊ ነው። የስብከት ዓላማ፣ ዝግጅት እንዲሁም አቀራረብ የመሳሰሉ በስብከት አገልግሎት ውስጥ ወሳኝ ነገሮች ናቸው። እነዚህም ነገሮች በትምህርቱ ውስጥ በሂደት የምታጠኗቸው ነገሮች ናቸው።

የኮርሱ ጥረት አድማጮች በተስተካከለ እውቀት እንዲሰበኩና መልዕክቱን በማጣጣም በትክክል እንዲያምኑ መርዳት ነው። ባልተስተካከለና በተዘበራረቀ መልኩ ስብከት የቀረበ እንደሆነ የመልዕክቱን ማዕከላዊ አቅጣጫ ለማስጨበጥ የታሰበው እውነት ስለሚፋለስ ስብከቱ ያለው ተአማኝነትና ተቀባይነት ይቀንሳል።

ስለዚህ ብቃት ያለውና የተሻለ መርህ የተከተለ የአሰባበክ ዘዴን ማዳበርንና በዘልማድ ከሚደረግ የስብከት አገልግሎት በመውጣት የተሻለ ሆኖ መቅረብና የእግዚአብሔርን መንግስት ሐሳብና ፈቃድ ለሰዎች ሁሉ መግለጽ ነው።

# ምዕራፍ 1 ስብከት እና ሰባኪ

## 1.1 የስብከት አስፈላጊነት

የስብከት ዘዴን(Homiletics) ማጥናት ስንጀምር ማስተዋል የምንጀምረው ጉዳይ ቢኖር ስብከት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ማዕከላዊ ስፍራ የሚይዝ መሆኑን ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ተናገረ ይባል ከነበረባቸው መንገዶች መካከል የነብያትና የካህናት ድንቅ የትጋት ስብከቶች ዋንኛውን ስፍራ ይዘው ይገኙ የነበር ሲሆን በአዲስ ኪዳን የምናየውም እውነታ የእግዚአብሔር ቃል በስብከት መልክ ሲቀርብና ህዝቡን ሲያንቀሳቅስ ነው። ማቴዎስ ወንጌሉን መፃፍ ሲጀምር *"መጥምቁ ዮሐንስ እየሰበከ መጣ"* ማቴ 3፡1 የሚል ማሳሰቢያ ተናግሯል። ከዚህም በኋላ የኢየሱስን በዲያብሎስ መፈተን ተናግሮ *"ኢየሱስ መስበክ ጀመረ"* ማቴ 4፡17 የሚል ቀጥተኛ ሐሳብ ይናገራል ይህም የሚያሳየን የስብከትን በጣም አስፈላጊነት ነው።

በጳውሎስ አገልግሎት ውስጥ ስብከት ትልቅ ስፍራ ነበረው ለጢሞቴዎስ ማስጠንቀቂያ አዘልና ምክር ሊሰጠው ይቆይና *"ቃሉን ስበክ"* በማለት መመሪያ ይሰጠዋል 2ኛ ጢሞ 4፡2 በሞኝነት ስብከት የሚያምኑትን ያድን ዘንድ እግዚአብሔር ደስ እንደሚሰኝ ጳውሎስ ያውቅ ነበር(1ኛ ቆሮ 1፡21) ስብከት ያላመነትን ለመድረስ ቅድሚያውን ስፍራ ሊይዝ የሚችል እንደሆነ እንረዳለን(ሮሜ 10፡14-15)።

በዚህ ምዕራፍ የስብከትን ጠቃሚነት ከተለያየ አቅጣጫ እንቃኛለን። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከቤተክርስቲያን እድገትና ተከላ እንዲሁም በድንቅ ከሚሰብኩ የተቀቡ አገልጋዮች ጋር ስብከት ቀጥተኛ ግንኙነት እንደነበረው እንገነዘባለን። በዚህ መሠረት ስብከት ሰዎችን ሁሉ በወንጌል ለመድረስ ግንባር ቀደም የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። ስብከት በየጊዜው ለሕይወታችን መስመር ቀጥተኝነት አስተዋጽኦ የሚያደርግና በየጊዜው ልባችንን የሚነካ ለእግዚአብሔርም ለመታዘዝ የሚያበቃ ተነሳሽነትን እንዲሰጠን የዘወትር ፀሎታችን ሊሆን ይገባዋል።

# 1.2 የአሰባበክ ስልት

ሆሚሌቲክስ የሚለው ቃል ጣምራ ትርጉም ካለው የግሪክ አዲስ ኪዳን ቃል የመጣ ነው። ሆሚሊቲክስ ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉምና ማብራሪያ ይህን ያህል ያነሰ ቢሆንም እንኳ ተግባራዊ ምልከታውን ያየን እንደሆነ ግን እጅግ ሰፊ ነው። ሆሚሌቲክ የሚዳስሳቸው ክፍሎች በተለይም ዝግጅትንና መልዕክት አቀራረብን ነው። በጥናት የተመሠረተ ሂደትንና መንፈሳዊ ገጽታን ባካተተ መልኩ የሚታይ ሆኖ የሰውንና የመለኮትን ነገሮች አጣምሮ በስብከቱ፤ በሰባኪው እንዲሁም በአድማጮች መካከል መግባባትን የሚፈጥር ጥበብ ነው።

## 1. የስብከት ጥበብ ያለው ዋጋ

የስብከት ጥበብ ጠቀሜታ አጠያያቂነት የሌለውና ሊረሳ የማይገባ ጉዳይ ነው። ያለ ስብከት ዘዴ መስበክ ማለት የአናፂ እቃዎችን ሳይዝ በባዶ እጅ የሚያምር የአናጺ የሥራ ውጤት ለማግኘት እንደመጠበቅ ነው። አንዳንድ ሰዎች ስለ አሰባበክ ዘዴ ምንም ግድ የለኝም እኔ ብቻ መልዕክትን ላቅርብ ይላሉ፣ ሌሎች ደግሞ የጥንት ሰባኪዎች ሐዋርያት የአተረጓጎም ስልትና የአሰባበክ ዘዴ አያወቁም ነበር ነገር ግን የእግዚአብሔር ክብር ብቻ ነበራቸው ይላሉ፤ እንዲሁም ሌሎች ጽንፈኞች የተማርኩትን የስብከት መርህ ሁሉ እግዚአብሔር አስረሳኝ ይላል፣ ይህ ሁሉ አባባል ግን በአንድነት ከእንዝላልነት ወይም ግድየለሽነት የመነጨ እና ለውጤታማ የስብከት ዘዴ ግድ ከማጣት የመነጨ ነው። ስብከት በወንጌል ዓለምን ለመድረስ ዋና መንገድ ከሆነ ጥሩና ውጤታማ ለመሆን ደግሞ የስብከትን ንድፈ ሐሳብ የምናጠናበት የስብከት ዘዴ ለእያንዳንዱ ሰባኪ ያስፈልጋል።

## 2. ስለ ስብከት ዘዴ የተሳሳቱ አመለካከቶች

በብዛት የሚሰነዘሩና ስለ ስብከት ዘዴ የሚነገሩ የተሳሳቱ አመለካከቶች መታረም አለባቸው፦

- የስብከቱን ይዘት በተመለከተ አስፈላጊ ዝግጅት ካደረገ የስብከት ዘዴው ወዲያውኑ በቅጽበት ሊመጣለት ይችላል ይላሉ ሆኖም ሰባኪው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ የስብከት ዘዴን እንደተማረ

እያጠና መቀጠልና ውጤታማ መሆን ይኖርበታል። ይህም የመንፈሳዊ ሕይወቱ ዝግጅት አንድ አካል ነው።

- ሁለተኛው የተሳሳተ አመለካከት ደግሞ ስብከት ዘዴ ዝግጅትና ጥናት ላይ ያተኮረ ሰው ሰራሽ ዘዴ በመሆኑ የመንፈሳዊን የስብከት ዝግጅት ገጽታ የሚያደበዝዝ ይሆናል። ተግባራዊ ጥናትና ዝግጅት ከመንፈሳዊ ዝግጅት ጋር በተቃርኖ የሚታይ ሳይሆን የማይነጣጠሉ የውጤታማነት ሁለት ክፍሎች ናቸው። ጥሩ መንፈሳዊ አቋም ያለውና ዝግጁ የሆነ ሰባኪ ያለዝግጅት መንፈሳዊ ብቻ ከሆነ ሰባኪና በዝግጅት ብቻ ተሞልቶ መንፈሳዊ ሳይሆን ከተገኘ ሰባኪ አንጻር ሲታይ እጅግ የተሻለ ነው።
- ሦስተኛው ስብከት ዘዴ ላይ የሚሰነዘር ስህተት ደግሞ ሰብአዊ የሆነ ችሎታና መለኮታዊ ብቃት በተናጠል የሚታይ እና በአንድነት ተጣምረው የሚታዩ የሰባኪ ውጤቶች አይደለም የሚል ነው። ሆኖም ግን የሰውን ችሎታና የመለኮትን ሥጦታ በአንድነት በማጣመር የሚገለጥ እንጂ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል(2ኛ ጢሞ 2፡15)።

## 3. የስብከትን ስልት የምናጠናባቸው መንገዶች

- ስብከት ዘዴ የምናጠናበት መንገድ በክፍል ውስጥ ወይም በርቀት ትምህርት መልክ መርሁን ማጥናትና ማንበብ ያስፈልጋል። ስለ ስብከት ዘዴ የተጻፉ ብዙ መጽሐፍት በልዩ ልዩ ቋንቋዎች አሉ እነርሱን ማንበብ እውቀትን ለማዳበር ይጠቅማል። ዋና የስብከት መጽሐፉችን ሊሆን የሚገባውን ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነው።
- የተለያዩ ጊዜ ላይ የተነሱ ድንቅ የሆኑ ሰባኪዎች የሕይወት ታሪክና ስብከቶቻቸውን ማጥናት ሌላኛው መንገድ ሲሆን ስብከትና ታሪኮቻቸውን በማንበብና በመስማት ዘዴዎቻቸውንና አስተሳሰባቸውን ማግኘት ይቻላል።
- የራስን ስብከት በማሰላሰል መለማመድ ለመሻሻልና ለበለጠ ዝግጅት ይጠቅማል። ይህ ደግሞ እንደሰባኪ ለማደግ አማራጭ የማይገኝለት ጥሩ መንገድ ነው።

- በስብከት ዘዴ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትና እርዳታ ለማግኘት የጠበቀ ጸሎት ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም የስብከትን ጥበብ እውነታዎች ቁልጭ አድርጎ ለማየት ይጠቅማል።

## 1.3 ስብከትና ትምህርት

ስብከትና ትምህርት የሚለያዩበትና የሚመሳሰሉበት ሁኔታ አለ፡- አንድነታቸው ሁለቱም የእግዚአብሔር ቃል መልዕክት መሆናቸው ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የአቀራረብና የሰሚዎቹ የመልዕክቱ ተቀባዮች ሁኔታ ነው። የሆነ ሆኖ ሁለቱም(ስብከትና ትምህርት) ይደጋገፋሉ። ስብከት ያነቃቃል፤ ትምህርት ያሰለጥናል ደቀመዝሙር ያደርጋል። ሁለቱም አስፈላጊዎች ናቸው።

### 1. ትምህርት

- ጠለቅ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥናትና ዝግጅት የሚጠይቅ ነው።
- ወጥነት ያለው መልዕክት ነው።
- የጥያቄና የመልስ ጊዜና ዕድል ይኖረዋል።
- ሁለቱም(አስተማሪውና ሰሚዎቹ) ተዘጋጅተው ይመጣሉ።
- ብዙ ጊዜ በዕድሜ በመረዳትና በትምህርት ደረጃ የሚቀራረቡ(ብዙ የማይራራቁ) ሰዎች ይገኙበታል።
- ብዙ ዝግህትና ሥልታዊ አቀራረብን ይጠይቃል።

### 2. ስብከት

- በዕድሜ፣ በጾታ፣ በኃይማኖትና በትምህርት ደረጃ የሚለያዩ ሰዎች በአንድነት ይካፈላል።
- እንደ ትምህርት ጠለቅ ያለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምርምርና ስልት ሳያስፈልገው ቀላል ባለ መንገድ ይቀርባል።
- በመደበኛ አምልኮ(አብዛኛውን ጊዜ) በልዩ ልዩ መነቃቂያዎችና በመሃ ስብከት ወንጌል(Crusade) ጊዜ ይቀርባል።

- በለቅሶ ቤት፣ በሰርግ ቤት፣ በቤት አምልኮ ፕሮግራም በተለያዩ የአገልግሎት ቡድኖችና በተለያዩ ክርስቲያናዊ ሕብረቶች(Fellowships) ይቀርባል።

| ተ.ቁ | ስብከት | ትምህርት |
|---|---|---|
| 1. | መልካም ዜና ማወጅ ነው፤ የመልካም ዜና መልዕክት ደግሞ ወንጌል ነው። | ዕውቀትን ለማስተላለፍ ነው፣ ዕውቀቱም ወንጌል ነው። |
| 2. | ዕቅድ ሰዎችን ለንስሃና በክርስቶስ እንዲያምኑ ጥሪ ማድረግ ነው። | ለመግለጽ፣ ለመተርጎምና ለማብራራት ነው። |
| 3. | ዕቅዱ የሰዎችን ትኩረት ወደ ክርስቶስ ለማድረግ ነው። | ዕቅዱ አማኞችን ደቀመዝሙርት ለማድረግ ነው። |
| 4. | ግቡ የጠፉትን ለመድረስ ነው። ስብከት ለዳኑትም ሊሆን ይችላል። | ግቡ አማኞችን በክርስቶስ ሙሉ ሰዎች ለማድረግ ነው። |

## 1.4 የሰባኪ ማንነት

የከበረውን የሕይወት ቃል የሚስብክ አገልጋይ ብቁ ሊያደርገው የሚችለውን መስፈርት ለማሟላት ትክክለኛ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ የመገኘት ጉዳይ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር ነው። መልዕክትና መልዕክተኞች ተነጣጥለው የሚታዩ ነገሮች አይደለም። በ1ኛ ጢሞ 4፡16 ስንመለከት ጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁ ለሆነው ለጢሞቲዎች "ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ በእነዚህም እና ይህን ብታደርግ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና ሲል ጥብቅ ማሳሰቢያ ሲሰጠው እናያለን። ከዚህ በመቀጠል ሰባኪው ምን ዓይነት ነገሮች ማሟላት እንዳለበት እንመለከታለን።

### 1. የኃጢአት ይቅርታ በማግኘት የዳነ መሆን ይገባዋል

ሰባኪው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው የጠበቀ ግንኙነት የተመሰረተ ልምምድ ሲኖረው ባሰበው መልክ እግዚአብሔር ለሌሎች የሚያስረዳበት ትክክለኛ ስዕል ይኖረዋል። አንድሰው ዳግም ተወልዶ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘቱ ውስጣዊ ጉዳይ ቢሆንም በሚኖረው ኑሮና በሚያፈራው ፍሬ እንዲሁም በአጠቃላይ አመለካከቱና መመዘኛው ልናውቀው እንችላለን(ሉቃ 7፡43፣ 2ኛ ቆሮ 4፡5-7)።

### 2. የቅድስናን ኑሮ የሚናፍቅ መሆን አለበት

በአገልግሎት ውስጥ ቅድስና እግዚአብሔርን መምሰል ዋና ነገር ነው። ሰባኪ ለማንኛውም ተመልካች ጤናማ የሆነ የሕይወት ምስክርነት ሊኖረውና ሊያሳይም ይገባል። ብዙ ሰባኪዎች መጥፎ ልምምድ ውስጥ ቀስ በቀስ ይገቡና የጥሞና ሕይወትን ያጣሉ፤ ከዚህም ጊዜ አንስቶ ከትንሽ እስከ ትልልቅ ኃጢአቶች ድረስ ያሉትን መቋቋም የሚችል ሕይወት ያጣሉ፣ በአድማጭ እይታ ፊት በአለባበስና በአነጋገር ጥበብ ብዛት የውስጥ ችግሮቻቸውን ለመሸፈን ይሞክራሉ(1ኛ ሳሙ 16፡7፣ 1ኛ ጢሞ 4፡12)። ለሚያምኑት ምሳሌ ሁን የሚል ምክር የምናነበው የዕለት ተዕለት ኑሮን በተመለከተ ነው(መዝ 16፡1-5፣ 2ኛ ተሰ 2፡9-12፣ 1ኛ ጴጥ 2፡11-16)። ቋሚና የተረጋጋ

የሕይወት አቋም የሌለው የወንጌል ሰባኪ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ቃልና አማኝነትን ያሰድባል(2ኛ ሳሙ 12፡14፣ ሮሜ 2፡21-24)።

### 3. የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ የተቀበለ መሆን ይኖርበታል

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን የእርሱ ምስክሮች በመሆን ንስሃና የኃጢአትን ይቅርታ እንዲሰብኩ ሲልካቸው አስቀድሞ ግን ያስጠነቀቃቸው ጉዳይ ቢኖር "ከላይ የሚመጣ ኃይል እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ቆዩ" ብሏቸዋል(ሉቃ 24፡47-49፣ ሐዋ 1፡8፣ 2፡4፣ 2፡38-39)። በብሉይ ኪዳን የነበሩ አገልጋዮች ሁሉ ለአገልግሎታቸው መከናወን ዋና ምክንያቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የነበራቸው የጠበቀ ግንኙነት ነው። መንፈስ ቅዱስ የአገልግሎት ችሎታንና ብቃትን ለሁሉም ሰጥቷል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር(ማቴ 3፡16፣ ዮሐ 3፡34፣ ሐዋ 2፡33)። በብሉይ ኪዳን በውስንነት በሰዎች ሕይወት ይገለጥ የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ውስንነት አልነበረውም። ዛሬም ለሚፈልግና ከእርሱ ጋር በስምምነት ለመስራት ለወሰነ ለማንኛውም አማኝ በማይቋረጥና በተከታታይነት ያለገደብም መንፈስ ቅዱስ አብሮ ይሠራል ለማንኛውም ሰባኪ መቅረት የሌሰበት እጅግ አስፈላጊ መሣሪያ መንፈስ ቅዱስ ነው(ሮሜ 15፡18፣ 1ኛ ቆሮ 2፡4፣ 1ኛ ተሰ 1፡5)። መንፈስ ቅዱስ ከሚሠጣቸው ሥጦታዎች አንዱና ዋናው የስብከት ጸጋና ችሎታ ነው።

### 4. ቃሉን ለመስበክ ከፍተኛ ፍላጎት ያለው

ድንቅ ስብከት የሚሰበከው ስብከት ባለው አገልጋይ እንጂ መስበክ በሚችል ብቻ አይደለም። ለሚጠፋ፣ የእግዚአብሔን ቃል ለተራቡ፣ ለተሰበሰበው ህዝብ ጥልቀት ያለው ፍቅርና ሸክም ኖሮት ለመስበክ የሚፈልግ አገልጋይ ውጤታማ ይሆናል። የመስበኩ ሥራ ግዴታ ሆኖበት ሳይሆን ሕይወትን የማዳን ተግባር እንደሆነ ሊታሰብ ይገባል። በልቡ ውስጥ የሚቀጣጠል ቅናት እውነተኛ ስሜትና እርምጃ እንድንወስድ የሚቀሰቅስ ነው። ብዙ ስብከቶች ውጤታማ ሳይሆኑ የሚቀሩት

ሰባኪዎች እውነተኛ ቅናት የጎደላቸው ስለሚሆኑ ነው። ስብከቱ በደንብ የተዘጋጀና በትክክል ለአድማጮች የቀረበ ሊሆን ይችላል ሆኖም የስብከትን ስራ ከመስራትና ኃላፊነትን ከመወጣት ያላለፈ ድርጊት ብቻ ይሆናል። ሕይወት የማይለውጥ የመከነ ስብከት እውነተኛ ካለመሆኑም በላይ የትክክለኛ ሰባኪዎችን ቦታ ቀድሞ የመያዝ አደጋም ነው።

## 5. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና የሚያገለግላቸውን ሰዎች የሚወድ ሊሆን ይገባል

አንድ ሰባኪ ሥር የሰደደና የጠለቀ የክርስቶስ ፍቅር ካልኖረው በስተቀር በር ተከፈተልኝ በማለት ብድግ ብሎ መስበኩ ውጤታማ አያደርገውም። የዚህ አገልግሎት አንቀሳቃሽ ሞተር የክርስቶስ ፍቅር ሲሆን ግቡ ደግሞ ተገልጋዮችን በፍቅር ወደ ክርስቶስ ማቅረብ ነው(ዮሐ 21፡15-19፣ ሮሜ 8፡35-39፣ 1ኛ ቆሮ 9፡16-22፣ 2ኛ ቆሮ 5፡14)። ሰባኪ መሆንን መውደድ አንድ ጥሩ ጎን ሆኖ የሚሰበኩ ሰዎችን መወደድ ደግሞ ሌላ ገጽታ ነው(ማቴ 14፡14፣ 15፡32፣ 20፡34፣ ማር 1፡41፣ 5፡19፣ ሉቃ 7፡13፣ 1ኛ ቆሮ 13፡1-8)።

## 6. የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ያስፈልጋል

የአሰባበክን ስልት ጠንቅቆ ማወቁ በራሱ ሊያመጣ የሚችለው ለውጥ አይኖርም፤ ሆኖም ሥርዓት ባለው መልኩ የተከማቸ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ጋር ሲገናኝ የሚጠበቀው ለውጥ መታየት ይጀምራል። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰባኪ ከፍተኛ ሥልጣን የሚሰጥና የትክክለኛ መረጃ ምንጭም ነው። ለመንፈሳዊ ትርፋማነት ሰባኪው በየእለቱ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በመመርመርና በማጥናት ለሰባኪነት ብቁ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል። መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የሕይወት ዘመን ሁሉ ቁርኝት እንጂ በስብከት ሰሞን ብቻ የሚጠና አይደለም። ለወቅቱና ለጊዜው የሚሆንን መልዕክት ማቅረብ የሚቻለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለው ትውውቅ የጎላ ሲሆን ነው(ምሳ 19፡2፣ ሆሴ 4፡4፣ ሐዋ 17፡11-13፣ 2ኛ ጢሞ 2፡15)።

# ምዕራፍ 2 የስብከት ዓይነቶች

የተለያዩ የስብከት ዓይነቶች አሉ። ዋና ዋና የሚባሉ የስብከት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፦

## 2.1 ርዕሳዊ ስብከት

ርዕሳዊ ስብከት ያለመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ድጋፍ ከስብከቱ ማዕከላዊ ሐሳብ መርጦ በመውሰድ የሚመሰረት ሆኖ ዋና ዋና ክፍሎቹም እያደጉ የሚሄዱት ማዕከላዊ ሐሳቡን በማጠናከር ነው። እያንዳንዱ ዋና ክፍል እየተያያዘና ንዑስ ደጋፊ ሐሳቦች እየሰራ ሲሄድ የተለያዩ ጥቅሶችን እየጨመረ ይሄዳል። ርዕሳዊ ስብከት ማለት ዋና ዋና ክፍሎቹ የሚደራጁት ከርዕሱ በመነሳት ሲሆን ከአውደ ምንባባዊ ወይም ጥቅስ መነሻነት ነጻ የሆነ ነው።

ርዕሳዊ ስብከት ከጥቅስ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ አንቀጽ አይነሳም ወይም አይጀምርም ስንል በርዕሳዊ ስብከት እንደ እግዚአብሔር ቃል ሳይሆን በሰባኪው ሐሳብ የተመሠረተ ነው ለማለት አይደለም። ነገር ግን በርዕሳዊ ስብከት የግድ መነሻውን ከአንድ ጥቅስ መጀመር ላይኖርበት ይችላል ለማለት ነው። ስብከቱ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ታራቂ የሆነ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረትም የተጠናከረ ነው። እያንዳንዱም ክፍል በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የተጠናከረ ነው። እያንዳንዱም ክፍል በእግዚአብሔር ቃል ማስረጃነት የተደገፈ ሆኖ ሊቀርብ ይገባዋል።

➢ **የርዕሳዊ ስብከት ምሳሌ**

ስብከት ምን መሆኑን ለመገንዘብ እንዲያስችለን አስተዋጽኦ በማውጣት መስራት ይኖርብናል።

ለምሳሌ ያህል “መልስ ያጣ ጸሎት” የሚለውን እንውሰድ፤ ርዕሱን ከሆነ ጥቅስ ልንወስድ እንችላለን ሆኖም አውደ ምንባቡን ተከትለን መስራት ማለት አይደለም። ከምናወጣው ርዕስ ዋና ክፍሎችንም እናገኛለን፤ በዚህ ጊዜ ለጸሎት መልስ ማጣት ዋና ምክንያት ምን እንደሆነ እናገኛለን። ርዕሱን በተመለከተ ቁጭ ብለን ስናሰላስልና ከእግዚአብሔር ቃልም ማሰብ ስንጀምር ጸሎት ሳይመለስ እንዲሁ የሚቀርባቸውን ምክንያቶች ልዩ ልዩ ሥፍራ ትዝ ይሉናል። ታዲያ

ሁሉምጥቅሶች ጸሎት ለምን መልስ እንደማያገኝ ሊነግሩን ይገባል(ምሳ 28፡9፣ መዝ 66፡18፣ ማቴ 6፡7፣ 1ኛ ጴጥ 3፡7፣ ያዕ 1፡67፣ 4፡3)። እነዚህን ጥቅሶች በማቀናጀት ትክክለኛ ርዕሳዊ ስብከት ለመፍጠር የተለያዩ ረጅም መጽሐፍትን መጠቀሙ አስፋላጊ ነው ለምሳሌ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ መዝገበ ቃላት በርዕሱ ዙሪያ የተፃፉ መጽሐፍትን ማንበቡ የበለጠ ይረዳል።

- የተሳሳተ ልመና ማቅረብ(ያዕ 4፡3)
- በልብ ውስጥ ያለ ኃጢአት(መዝ 66፡18)
- የእግዚአብሔርን ቃል መጠራጠር(ያዕ 1፡6-7)
- ከንቱ ውዳሴ(ማቴ 6፡7)
- ለእግዚአብሔር ቃል አለመታዘዝ(ምሳ 28፡9)
- በትዳር መካከል መቀባበል መታጣት(1ኛ ጴጥ 3፡7)

### ➢ የርዕሳዊ ስብከት ግምገማ

እንደ ዲ.ኤል መዲ ያሉት ታዋቂ የአሜሪካን ሰባኪዎች ብቸኛው ወጤታማ መንገድ አድርገው ይጠቀሙበት የነበረ የስብከት ዓይነት ርዕሳዊ ስብከት ነበር። ሌሎች ደግሞ አውደ ምንባባዊና ገለጻዊ ስብከት የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ብለው ያምኑ ነበር።

**የርዕሳዊ ስብከት ጠቀሜታ**

- አንድነትና ወጥነት ያለው ነው። ተጠናቆ ያለ ርእሳዊ ስብከት ማዕከላዊ ሐሳቡ ከርዕሱ ጋር በታራቂነት የሚቀጥል ሆኖ የሐሳቡም ፍሰት አንድ ሐሳብ ላይ ያተኮረ ነው። ወጤቱ ላይ ያተኮረ ርዕሳዊ ስብከት ኃይለኛ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችልና የሰሚዎቹን ስሜት የሚቆጣጠር ነው። ቀጥተኛ የሆነ የባህርይ ለውጥ ለማምጣት ወንጌላዊያን ሰባኪዎች ቢጠቀመበት ፈጣን ለውጥ ለማምጣት ያስችላል።

- አንድን እውነት ማዕከል ያደረገ ጠንካራ መልዕክት ስለሚያስተላልፍ በቀላሉ ለመረዳት ይጠቅማል። ስብከቱ ከጅማሬው እስከ መደምደሚያው ድረስ እንዴት እያደገ እንደሚሄድ ህዝቡ በቀላሉ ሊረዳው ይችላል።

**የርዕሳዊ ስብከት ደካማ ጎን**

- ብዙ በማጥናትና በመዘጋጀት ፈንታ እንዲሁ ነካ ነካ በማድረግ ጠቃሚ ያልሆነ ተራ እና እዚህ ግባ የማይባል ስብከት ለማቅረብ የተጋለጠ ነው። ስብከቱ በራሱ የተሟላና በጊዜም የተገደበ ነው ሆኖም አንዳንዴ ያልተሟላና የማይገጣጠም የተበጣጠሰ ሐሳብ ወርወር አድርጎ የሚወርዱ ብዙዎች ናቸው። ይህም የሆነው ርዕሳዊና በሰባኪው ምርጫ የተመሠረተ በመሆኑ ነው።
- የግል አስተሳሰብን ወይም ፍላጎትን ለመጫን የተጋለጠ ነው። በዚህ ጊዜ የመጨረሻው ሥልጣን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ ይቀርና የግለሰቡ የአስተሳሰብ ሚዛን የላቀ ይሆናል። የምናነበው ወይም የምንሰብከው የምንባብ ክፍል ከመላው መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ጋር ምን ያህል በታራቂነት ፍሰቱን ቀጥሏል? የሚለው ይቀርና ከእኛ የስነ መለኮት አስተሳሰብ ጋር በግድ እንዲገጥምልን ክፍሉን እናሰቃየዋን። ይህ ደግሞ እያደገ ከሄደ ለስህተት ትምህርት የሚያጋልጥ ይሆናል።
- ለያዝነው ርዕስ ወይም የምንባብ ክፍል ታማኝ አለመሆን፤ ብዙ ሰባኪዎች ከያዙት ርዕስ ጋር ስለሚሄድ ብቻ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለይስሙላ ያነቡትና ከዚያ በኋላ በስብከታቸው ጊዜ ግን ዞረው አያዩትም። የራሳቸውን ኮተት የተሞላ ሐሳብ ሲዘባርቁ ቆይተው ታማኝነት የጎደለው ስብከት ሰብከው ይወርዳሉ።
- ሌላው አደጋ ደግሞ የራስን ክብር ማስጠበቅ ነው። ይህ ሲባል አንድ እውነት ቀድሞ በተነገረበት ተመሳሳይ መንገድና በመንፈስ መናገር አለመፍቀድና በራስ አመለካከት አድማጭን በማስደነቅ ትኩረትን ወደራስ ለመሳብ የሚደረግ ጥረት ነው። ከመላ የመጽሐፍ

ቅዱስ እውነት ጋር ሊጣጣም በማይችል መልኩ ራስን ከሌሎች አልቆ ለማሳየት የሚደረግ ክብር ፍለጋ ነው።

## 2.2 አውደ ምንባባዊ ስብከት

አውደ ምንባባዊ ስብከት ከርዕሳዊና ገለፃዊ ስብከቶች ጋር አንድ የሚያደርገው ነጥቦች አሉት። ልክ እንደ ርዕሳዊ ስብከት ትምህርቱን የሚያገኘው ከምንባበ ነው ሆኖም አስተዋጽኦው እየተጠናከረና የሚብራራልን ነጥብ የሚደግፉ የተለያዩ ተዛማጅ ጥቅሶችን መጠቀም ይቻላል። ዋና ሐሳቡ ግን መውጣት ያለበት እዚያው የምንባብ ክፍሉ ውስጥ እንጂ ተስማሚ ምክንያት ይሆናል ተብሎ ከሌላ ቦታ መውሰድ የለበትም።

የአውደ ምንባባዊ ስብከት ዓላማ ማብራሪያ መስጠት እስከሆነ ድረስ ገለጻውም ማዛመዱም ሁሉ የሚሰራው በዚህ በተመረጠው የምንባብ ክፍል ብቻ ነው። አውደ ምንባባዊ እና ገለፃዊ ስብከቶች የሚለያዩት በአውደ ምንባቡ ርዝማኔና ማብራሪያ ካልሆነ በስተቀር የተቀራረበና የተዛመደ ግንኙነት አላቸው፤ ሆኖም ገለፃዊ ስብከት ማዕከላዊ ሐሳቡን የሚያገኘው ከጠቅላላው ሐሳቡን ከሚደግፉ ክፍሎች እንጂ እንደ አውደ ምንባባዊ ስብከት ከውስን የምንባብ ክፍሉ ብቻ አይደለም። ለአድማጮች በሚገባ መልኩ የክፍሉን ሐሳብ ማብራራትና ከሕይወታቸው ጋር ማዛመድም ያስፈልጋል። የአውደ ምንባባዊ ስብከት አስተዋጽኦ(ማውጫ) ቃላቶች እንኳ ሳይቀሩ መወሰን ያለባቸው በምንባብ ክፍሉ መሠረት ነው። አስተዋጽኦው ሲጻፍ ቅደም ተከተሉን ጠብቀን ማቅረብ እንጂ የምንባብ ክፍሉ ከሚሰጠን ቋንቋ ወይም አረፍተ ነገር ውጭ በራሳችን ዘመንኛ ቋንቋ ገለባብጠን ማቅረብ የለብንም። ዓላማችን በምንባብ ክፍሉ ያለውን እውነት አንጥረን በማውጣት ለሰሚዎች ግልጽ ማድረግ እንጂ በመጀመሪያው ፀሐፊ አዕምሮ ያልነበረን አዲስ እውነት መፍጠር አይደለም።

- **የአውዳዊ ስብከት አስተዋጽኦ ምሳሌዎች**

የመጀመሪያውን ምሳሌያችንን ከዕዝ 7፡10 ላይ እንውሰድና አስቀድመን ክፍሉን እናንብብ። *"ዕዝራ የእግዚአብሔርን ህግ በማጥናትና በማድረግ ለእስራኤልም ሥርዓቱንና ህጉን በማስተማር ራሱን ፈጽሞ ሰጥቶ ነበር።"* አንዳንድ ትርጉሞች ልቡን አዘጋጅቶ ነበር ይላሉ የምንባብ ክፍሉና ቁጥሮቹ የሚያጠነጥኑት በእዝራ የልብ ዝግጅትና የልብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው። ስለሆነም የሚከተሉትን ዋና ክፍሎችና ቁጥሮች እናወጣለን፦

- የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ ተዘጋጅቶ ነበር እዝራ የእግዚአብሔርን ህግ ለማጥናት የተዘጋጀ ነበር።
- ለእግዚአብሔር ቃል ለመታዘዝ ተዘጋጅቶ ነበር ህጉን ለማድረግ የተዘጋጀ ነበር።
- የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ተዘጋጅቶ ነበር ለእስራኤል ሥርዓቱንና ህጉን ለማስተማር ራሱን ፈጽሞ ሰጥቶ ነበር።

በእነዚህ ማዕከላዊ ሐሳቦች ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ቁምነገር የዕዝራ የልብ ዝግጅት ነው። በመጀመሪያው ዋና ክፍል ውስጥ የምናየው ሐሳብ የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ እዝራ የነበረውን የልብ ዝግጅት ነው(ዕዝ 7፡10)። ለዚህ ሐሳብ ዝርዝር ማብራሪያ አይሰጥም ስለሆነም የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ ስለሚደረግ ዝግጅት ማብራሪያ በመስጠት የሚያግዙ ሌሎች ክፍሎችን በመፈለግ ሐሳቡን ልናጎለብተው ያስፈልጋል። በዚህ በዕዝ 7፡10 አውደ ምንባብ ውስጥ ቁጥር 6 እንዲህ ይላል *"እርሱም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ስሙሴ የሰጠውን ህግ በሚገባ የሚያውቅ የህግ መምህር ነበር"* እንዲሁ ቁጥር 11፡12 እና 21።

"የእግዚአብሔር ህግ አስተማሪ" ይለዋል በቁጥር 14 እና 25 ላይ ስናነብ ደግሞ በፋርስ ንጉስ አርጤክስስ ዘንድ ሳይቀር ዕዝራ የህግ መምህርና የህግ አዋቂ መሆኑ ይታወቃል። ዕዝራ በነበረው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሳይገደብ የበለጠ ህጉን ለማወቅ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር። ይህን ደግሞ ያደረገው በአረማውያን በማያምኑ) መካከል ነበር። ዕዝራ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚያጠና አንዳንድ መዝሙራትና የታሪክ መጽሐፍት በመደነቅ ይጽፋሉ በኢያሱ 1፡8 ላይ *"ይህ የህግ*

*መጽሐፍ ከአፍህ አይስይ በውስጡ የተፃፈውን ሁሉ በጥንቃቄ እንድትፈጽመውም ቀንም ሆነ ሌት ከሐሳብህ አትስደው ይህን ካደረግህ ያሰብኸው ይቃናልሀል ይሳካልም" ይላል* እንዲሁም ምሳሌ 8፡34-35 ላይ *"በያዕስቱ ደጃፌ ላይ የሚጠብቅ በበራፉ ላይ የሚጠባበቅ የሚያዳምጠኝ ሰው ብሩክ ነው የሚያገኘኝም ሁሉ ሕይወትን ያገኛል ከአዝኢአብሔርም ዘንድ ሞገስን ይቀበላል"* እንዲሁም ኤር 29፡13 ጌታን የሚሰማ ሁሉ ልቡን እንደሚፈትሽ ይናገራል *"በፍፁም ልባችሁ ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ"* እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ የሚነግሩን ዕዝራ ልቡን የነኩትና ያዘጋጁት ለእንደዚህ ዓይነት ተግባር መሆኑን ነው። ከባቢሎን እስከ ኢየሩሳሌም የሥራ ውጤት ያደረሰው የልቡን ናፍቆትና ዝግጅት እንዲሁም ተግባራዊ ርምጃ መውሰዱ ነው።

- **የአውዳዊ ስብከት ግምገማ**

በፍላጎት ደረጃ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰባኪዎች አውዳዊ ስብከትን እንደ ብቸኛ አውደ ምንባባዊ ማብራሪያ መንገድ አድርገው ይወስዳሉ። የዚህ አስተሳሰብ አንዱ አዎንታዊ ገጽታ ግድ የለሽነትና የሐሳብ መቆራረጥን ለማስቀረት መርዳት ነው።

**የአውዳዊ ስብከት ጠቀመታ**

አውዳዊ ስብከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ትምህርቱም ይሁን ዋና ክፍሎቹ በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚወጡ በመሆናቸው ሰሚዎችም ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እየተሰበከ፣ እየተብራራ እንደሆነ እንጂ ሰባኪው የሆነ ርዕስ ይዞ የመሰለውን ወይም የግል ልምምዱን እየተናገረ አለመሆኑን ይረዳሉ።

የተለየ ብቃቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለጻ የሚሰጥበትና የታማኝነት ባህርይ የሚንፀባረቅበት የሥብከት ዓይነት በመሆኑ ነው። አውዳዊ ስብከት በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን የተቃኘ ነው። በዚህም ምክንያት አማኞች የተሻለ የእግዚአብሔር ቃል መረዳት እንዲኖራቸው ይረዳል መጽሐፍ ቅዱስን በትክክለኛ የአተረጓጎም መንገድ ማብራራት ስሚዎች የተሻለ መረዳት

እንዲኖራቸው ይረዳል። ይህም ብቻ ሳይሆን ከብዙ ዓመታት በኋላ እንኳ የማይረሳና የሚታወስ መልዕክት በሰው ለማስቀመጥ ይረዳል። አውዳዊ ስብከት ቅዱስ ቃሉ ላይ እንደማተኮሩ መጠን ትንቢታዊ ቅኝት ያለው ሊሆን ይችላል።

አውደ ምንባቡ እየተብራራ እያለ ሰሚዎቹን ቢጎረብጣቸው፣ ቢያሳምማቸው ሰባኪውን ማንም ሊኮንነው አይችልም ምክንያቱም ጥንት የተፃፈ ቃል ነውና እግዚአብሔር ሰዎችን እየተናገራቸው መሆኑ ግልጽ ነው።

**የአውዳዊ ስብከት አሉታዊ ጎን**

ከጠንካራ ጎኑ ባሻገር ደካማ ጎኖችም አሉት ይኸውም በአውዳዊ ስብከት ሰባኪው በያዘው የምንባብ ክፍል ከተካተቱት ዋና ሐሳቦች ወይም ነጥቦች ውጭ የራሱን አመለካከትና አስተሳሰብ ሊጨምርበት ይችላል። ሌላው ችግር ደግሞ በኦሪጅናል ቃሉ ውስጥ የሌለን ወይም ያልተጻፉትን ቃላት በመጨመር የተለየ ትርጉምና ፍልስፍና ወስጥ በመግባት የራሱን የሞቀ ስሜት መከተል ነው። ሌላኛው ችግር ደግሞ ለሰሚዎች ጠቀሜታ የማይሰጥ ከንቱ ሐተታ መስጠት ነው። ዋና ነጥቦችን በማብራራት ቀላልና ግልጽ ስሚዎችን የሚያንጽ ትምህርት ይሁን እንጂ ሌሎችን ተቀጽላ ሐሳቦችና ሐተታዎች በሌላ መድረክ ለሌላ ተግባር ማቆየት ይቻላል።

# 2.3 ገላጭ ስብከት

ገላጭ ስብከት ከምንም ነገር በላይ ውጤታማ የመድረክ አገልግሎት ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ለህዝቡ ማስተማርንና ማብራራትን በውስጡ የያዘ የንግግር ክፍል በመሆኑ ነው። የገላጭ ስብከት ዋንኛ ትኩረት መጽሐፍ ቅዱስና ተገልጋዩ ህዝብ ነው። ስለ ገላጭ ስብከት የሚሰጡ ብዙ ዓይነት ትርጉሞች አሉ፣ ከብዙዎችም ትርጉሞች አንዱ የሚከተለው ነው። *“የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ ክፍል ማዕከላዊ ሐሳብን ትክክለኛ የአተረጓጎም ሥርዓት ተከትሎ ከወቅታዊው ሕይወት ጋር በማዛመድ ማዕከላዊ ሐሳቡን ማግኘትና ውጤት ሊያስገኝ በሚችል የተቀናጀ ሐሳብ የሰሚዎችን ወይም የአድማጮችን የመረዳት ብቃት ለማሳደግ እና በባህሪያቸውም እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የልብ መቃናት እንዲያድጉ መርዳት ነው።”*

የገላጭን ስብከት ትርጉም መሠረታዊ አወቃቀር ወይም ይዘት ለመገንዘብ ወደ ትርጉሙ እንደገና መመለስና መመልከት ያስፈልጋል።

ገላጭ ስብከት የመጽሐፍ ቅዱስ የስብከት ክፍል ማዕከላዊ ሐሳብን አሁን ከምንኖርበት ዘመን ወይም ጊዜ ጋር ያገናዝባል። ይህን ማዕከላዊ ሐሳብ ለማግኘት ግን ትክክለኛ የአተረጓጎምን ሥርዓት ወይም ስልት መከተል ያስፈልጋል። የሐሳብ ፍሰቱ የሚተላለፈው ደግሞ አጥጋቢ የሆነ የሰላም ግንኙነት በመፍጠርና ወደ አድማጮች የልብ መረዳት ማሳደግ እንዲሁም እግዚአብሔርን እየመሰሉ የሚያድግ የባህሪይ ለውጥ በማምጣት ነው።

ጀምስ ብራጋ የተባሉት የስብከት አዘገጃጀት ፀሐፊ ገላጭ ስብከት መሆን ያለበት ነገሮች ብለው የሚከተሉትን አስፍረዋል።

- ገላጭ ስብከት ውጤታማ የመድረክ አገልግሎት ተብለው ከሚፈረጁ የፑልፒት /አትሮንስ/ አገልግሎቶች ግንባር ቀደም የስብከት ዘዴ ነው።
- ገላጭ ስብከት የውስጥ ይዘቱ ከትርጉሙ የሚነሳ ወይም የሚመሠረት ክፍል ነው።
- ሁሉም የገላጭ ስብከት አስተዋጽኦ የሚመጣው ከዚያው የምንባብ ክፍል ነው።

- ሁሉም የአስተዋጽኦ ክፍሎች ሐሳብ እየተያያዘና እያደገ የሚሄድ መሆን አለበት።
- የገላጭ ስብከት ዓላማ ወይም ተግባር የምንባብ ክፍሉን በታማኝነት መግለጥ ፣ ማብራራት ነው።

የገላጭ ስብከትን አስተዋጽኦ ስናዘጋጅ ልንከተላቸው የሚገቡ መርሆዎች

- የመረጥነውን የምንባብ ክፍል በመረጋጋት ደጋግሞ ማንበብና የክፍሉን ዋና ትምህርት ማግኘት ያስፈልጋል። በዚህ መርህ ውስጥ ሰባኪው የተሰበሰበና የተረጋጋ መንፈስ ኖሮት በጸሎት የተደገፈ በቂ ዝግጅት የሚያደርግበት ጊዜ ነው።
- በምንባብ ክፍሉ በተደጋጋሚ የተገለጡ ቃላት ወይም ሐረጎች ሰየአስተዋጽኦ ዋና ክፍላችን ልናገኛቸው ስለምንችልና የተለየ ጠቀሜታ ሊኖራቸው ስለሚችል በጥንቃቄ ማጤን ጥሩ ነው።
- አንዳንድ ጊዜ አስተዋጽኦው ከገላጭ ስብከቱ ክፍል የሚወጣ ሆኖ ከምንባብ ክፍሉ የተለየ ሊሆን ይችላል።
- በምንባቡ ክፍል ውስጥ የሚታዩ እውነታዎች አካሄድ በራሱ የአስተዋጽኦውን ዋና ክፍል ሊወስነው ይችላል። ይህም የሚሆነው በምንባቡ ውስጥ ጎልቶ የሚታየውና ቅደም ተከተሉን እየጠበቀ የሚቀጥለው እውነት ራሱ አስተዋጽኦ ነው።
- የገላጭ ስብከትን አስተዋጽኦ አስተዋጽኦ ለማውጣት ሁለትና ሦስት ወይም ከዚያበታች የሆኑ ተዛማጅነት ኖሯቸው ግን የተለያየ ስፍራ ላይ የሚገኙ የምንባብ ክፍሎችን በአንድ ላይ መውሰድ ሊኖርብን ይችላል።

## ➢ የገላጭ ስብከት ጠንካራና ደካማ ጎን

***የገላጭ ስብከት ጠንካራ ጎን***

የዚህ የስብከት ዓይነት አዎንታዊ ጎኑ ብዙ ነው፤ ለራሱ ለሰባኪው ለአገልግሎቱና በተናጠልም ይሁን በህብረት ለሚሰሙ አድማጮች ሁሉ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። በመጀመሪያ

ደረጃ ሰባኪው የገላጭ ስብከትን ለማዘጋጀት ቁጭ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የሚጠበቅበት ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ትክክለኛ የአተረጓጎምን ሥርዓት ተከትሎ3የምንባብ ክፍሉን ሐሳብ ከአድማጮቹ ሕይወት ጋር ማገናኘት መጀመር አለበት። የገላጭ ስብከት የሚከተሉ ሰባኪዎች ከጌታ ጋር ያላቸው ግንኙነት እየጠለቀ የሚሄድ ከመሆኑም በላይ የስብከት አገልግሎታቸው እያደገ ይሄዳል። ሰባኪው ቀጥተኛ የእግዚአብሔርን ቃል ትርጉም የያዘ ንግግር ስለሚያደርግ ከፍተኛ ሥልጣንና የመተማመን ድፍረት እንዲኖረው ያደርጋል። ቃሉን ለሚሰብኩ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ትክክለኛ ፍፃሜ ስለሚያገኝ የአገልግሎቱ እውነተኛነት እያደገ ይሄዳል(ኢሳ 55፡11፣ ማር 16፡20)። ቃሉን ሲሰብክ ምልክቶች መታየት ይጀምራሉ ከዚህም ሌላ አድማጮች እየሰሙ ያሉት የግለሰብ ሰባኪዎችን የግል አመለካከት ወይም ፍልስፍና ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በትክክል ይገነዘባሉ። በዚህም የእግዚአብሔር ቃል ጥማታቸውን በቀላሉ ለማርካት ዓይነተኛ መንገድ ይሆንላቸዋል። የገላጭ ስብከት አድማጮች ማመዛዘን እንዲችሉ የሚረዳ መንገድ ነው። ህዝቡ ለሰማው ቃል ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ እንዲሆን የሚረዳና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትም እንደ ሞዴል ወይም ጥሩ ምሳሌ የሚወስድ የስብከት ዓይነት ነው።

***የገላጭ ስብከት አሉታዊ ጎኑ***

ብዙ ማብራሪያና የገለፃ ብዛት ሕይወት ለዋጭ ወደሆነው ተጨባጭ የተግባራዊ የዕለት ሕይወት ሳይመለስ የመቅረት ችግርና ከማብራሪያ ብዛት አሰልች ባህርይ ሊኖረው ይችላል። በማብራሪያው ውስጥ ድንገት ሌሎችም ዓይነት እይታዎች ለሰባኪው ብልጭ ስለሚሉለት የመወሰድና የመደናገር አበይት ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ለማጠቃለል ያህል በዚህ ክፍል እንዳየነው የገላጭ ስብከት ዓይነት ቀላልናለመስበክም የሚመች ነው። ሌላው የገላጭ ስብከት ጥቅም ደግሞ ከሌሎች የስብከት አይነቶች ጋር ሲተያይ የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለማድረግ ይረዳል።

# ምዕራፍ 3 የስብከት ዝግጅት እና አቀራረብ

## 3.1 የስብከት ዝግጅት

የስብከት አዘገጃጀት(Sermon) የሚለው ሥርወ ቃል የመጣው ከላቲን ሲሆን ትርጉሙም *“ወሬ፣ ንግግር፣ መነጋገር”* የሚል ሐሳብ አለው። የስብከት አዘገጃጀት የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሳብና ታማኝነት ሳያፋልስ የሚቀርብ እንጂ የስብከት አወቃቀር ሂደት ብቻ ሆኖ የሚቀር አይደለም። የስብከት አዘገጃጀት ማለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ሆኖ መግቢያ፣ መንደርደሪያ፣ የዋናው አካል ክፍሎች፣ እና መደምደሚያ ያለው ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ያለው፣ ማብራሪያ፣ ምሳሌ እንዲሁም ምክንያታዊ የባህሪይ ስምምነት ያለው ቅደም ተከተል የጠበቀ፣ እድገት የሚያሳይና መጨረሻ ያለው ነው።

በእርግጥ ከላይ ለስብከት አዘገጃጀት እንደተሰጠው ትርጉም ያህል ሥራው ውስብስብና አስቸጋሪ አይደለም። የአንድ ውጤታማና ዋጋ ያለው የሕይወት ስኬት ምክንያት ሲመረመር የተደራጀ እቅድና ቅርጽ ያለው የተዋቀረ አሠራርን የተከተለ እንደነበር መረዳት እንችላለን። ይህ የሚሰራው ለስብከት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሕይወት ዘመን ክንውኖች ነው። ቅንጅትና ተያያዥነት የሌለው ስራ ውበት ከማጣቱም ሌላ ረጅም እድሜ ማስቀጠር የማይችል ተልካሻ ሥራ ይሆናል።

### ➢ የስብከት ግብዓቶች

ጥሩ ስብከት ለማዘጋጀት በምናስብበት ጊዜ ለዝግጅታችን ውጤታማነት የሚረዱንን ምንጮች ማሰብ የግድ ነው። ለዚህም የሚረዱን ነገሮች ከብዙዎች ዋና ዋናዎች የሚከተሉት ናቸው።

- መጽሐፍ ቅዱስ፡- በእርግጥ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ የሆነ ሰው ያለመጽሐፍ ቅዱስ ሊሰብክ አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ሐሳብ የገለፀበት መጽሐፍ ነው። ስለዚህ የስብከት ቀዳሚ ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሰባኪ ጥሩ ስብከት ለማቅረብ የሚችለው ስለዚህ መጽሐፍ በቂ እውቀት ሲኖረው ነው። “ጥራዝ ነጠቅ”

ሰባኪ ውጤት ካለማምጣቱም በላይ የተሳሳተ ትምህርት ወደ ሰሚዎች ሊያስተላልፍ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት የማይገኝበት በእምነትም ጉዳዮች የመጨረሻው ባለሥልጣን እንደሆነ ማመን ለሰባኪው አማራጭ የሌለው እውነት ነው። እንዲህ መሳይ አመለካከት ካለው ደግሞ ሰባኪው የዚህን መጽሐፍ እውነት በግል ሕይወቱ መለማመድ ይጀምራል። እውነት የሚኖረው ትክክለኛ አስተሳሰቡና ድርጊቱ ነው።

- የመንፈስ ቅዱስ አብርሆት፦ መንፈስ ቅዱስ ለሚመጡ ሰዎች የሚሰጠውን የአብርሆት መልዕክት መቀበል ያስፈልጋል።
- የነገረ መለኮት መጽሐፍትን አዘውትሮ ማጥናት አንዱ የስብከት ምንጭ ሊሆን የሚችል መንገድ ነው። ይህ ሲባል ጥንቃቄ የሚያሻውና ከመንገድ የወጡ አንዳንድ ለዘብተኛ የስነመለኮት አስተሳሰቦችን ጠጥተን ስተን እንዳናናሳስት መርጠንና ተጠንቅቀን የማንቡብን ልማድ ማዳበር ይገባናል።
- በተለያዩ እውነተኛ አማኞች የተጻፉ ልዩ ልዩ የጥሞናና ክርስቲያናዊ ትምህርቶችን የያዙ መጽሐፍት ለስብከት ጥሩ እይታ ሊፈጥሩ ይችላሉ።
- የተለያዩ ሰባኪዎችን ስብከት ማንቡብ፣ ማድመጥ፣ ማየትና መከታተል ይጠቅማል። ይህ ሲባል ግን ምኑም ሳይቀር ገልብጠን ወስደን በሌላ ቦታ እንድንሰብከው ይረዳል ማለት አይደለም፤ ይህ ኩረጃ ነው። ደግሞም ለውጥና መነካት አያመጣም።
- የቃላት መፍቻ መዝገበ ቃላት እና ሌሎችንም ምንጮች ስብከታችንን ለማዳበር ይረዱናል።

## ➢ የስብከት እድገት

ስብከትን በማሳደግ ሂደት ውስጥ ሰባት መሠረታዊና ቁልፍ የሆኑ ሐሳቦች አሉ፡-

- የመጀመሪያው የምናስተምረውን ትምህርት ወይንም ዋናውን ሐሳብ የመምረጥ ሂደት ሲሆን ይህም የማሰስ ደረጃ ተብሎ ይጠራል። ይህንን ደረጃ ሰባኪው በጽኑ ጸሎትና በማሰላሰል ጊዜ የሚወስድበት የእግዚአብሔር ሐሳብ ለህዝቡ ምን እንደሆነ የሚረዳበት መልዕክት ለመቀበልም በሚያስችል የሕይወት አቅጣጫ ራሱን የሚያቀይበት ደረጃ ነው።

- ሁለተኛ ከብዙ ጸሎትና ጽሞና ጊዜ ቀጥሉ የሚመጣው ደረጃ ደግሞ የስብከቱን የምንባብ ክፍል መምረጥ ሲሆን ይህም የማገናዘብ ደረጃ ተብሎ ይታወቃል። የመረጠውን የትምህርት ሐሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተስማሚ የምንባብ ክፍል ይመርጥለትና የስብከት መዋቅሩን ሐሳብ ማለም ይጀምራል።
- ሶስተኛ የስብከቱ ዋና ሐሳብ ወደምን አቅጣጫ ማተኮር እንደሚገባው የሚወስንበት ጊዜ ሲሆን አቅጣጫ የማስያዝ ደረጃ ተብሎ ሊጠራ ይችላል።
- ከዚህ ቀጥሎ ስብከቱን በማዋቀርና ቅርጽ በማስያዝ ጠንከር ወዳለ ሀሳብ የሚገባበት ሂደት ሲሆን የቅንጅት ደረጃ ይባላል።
- ከመዋቅራዊ ቅንጅት በመቀጠል አስፈላጊ የስብከት ማሚያዎች እየፈለገ የሚያጠናክርበት ሂደት ደግሞ የማስፋፋት ደረጃ ይባላል።
- ከላይ በተዘረዘሩት ደረጃዎች ያለፈው ስብከት በትክክል የተዋጣለት ሥራ የተሠራ ወይም የተሳሳቱ ነገሮች አካቶ እንዳይሆን አጠቃላይ ፍተሻ የሚደረግበት ደረጃ ነው ይህም ስብከትን የመፈተን ደረጃ ይባላል።
- በሁሉም ዓይነት ደረጃ ያለፈ ስብከት መጨረሻ ላይ ቃል በቃል ማስታወሻ ደብተር ላይ ይጻፍና ይሠፍራል፣ ይህም የማረም ወይም የመተየብ ደረጃ ተብሎ የሚጠራው ነው።

## ➢ ለስብከት ዝግጅት የሚረዱ ነገሮች

### 1. ጸሎት

በሰባኪው ሕይወት ቁልፍ እሴት ወይም ዋጋ ያለው ጉዳይ ቢኖር ጸሎት ነው። ሆኖም ይህ ጸሎት ያለመንፈስ ቅዱስ ህልውና ድካም የተሞላበት ነው። በሰባኪው ሕይወት የማነጽ ተግባር ይፈፀማል። በይሁዳ መልዕክት ቁጥር 20 ላይ ሁሉም አማኞች *"በመንፈስ ቅዱስ እያዋስያችሁ"* የሚል ማሳሰቢያ ሲጣቸው እናያለን። በመንፈስ ቅዱስ መጸለይን አገልጋይ ከማንም ሰው በላይ አጥብቆ መለማመድ አለበት ሌላው ወሳኝ የመንፈስ ቅዱስ ተግባር ደግሞ በሰባኪው ጸሎት

ውስጥ ምልጃን ማድረግ ነው። ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰላከው ደብዳቤ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ የምልጃ አገልግሎት ምን እንደሚመስል ይገልጣል።

*"እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጽ በማይችል መቃተት ስለእኛ ይማልድልናል"*(ሮሜ 8፡26-27)። ይህ የምንባብ ክፍል እንደሚነግረን መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሆኖ በፀሎታችን አማካኝነት ስለሚሠራው ነው እንጂ ከእኛ ውጭ በሆነ መልኩ ለብቻው ወደ እግዚአብሔር ይፀልይ ማለቱ አይደለም። በታሪክ የሚታወቀው ሰባኪ ጆናታን ኤድዋርድስ «ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር የበቀል እጅ» የተሰኘውን ስብከቱን ከመስበኩ በፊት ከምግብ ፣ ከውኃ እና ከእንቅልፍ ሁሉ በመታቀብና በመፆም ለሦስት ቀንና ሌሊት ያህል አከታትሉ በመንፈስ ቅዱስ ፀለየ የምልጃውም ዓላማ «እንግሊዝን ስጠኝ» የሚል ነበር ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር ክብር በፊቱ ማብራት ጀመረ ወደ ስብከቱም ቦታ ሄደ መድረክ ላይ ቆመ፤ ጆናታን ኤድዋርድስ አንድ ቃል ከመተንፈሱ በፊት በጉባኤው አስደናቂው የእግዚአብሔር ህልውና ወረደ መስበክ ስጀመረበት ጊዜ ሊከሰት የቻለውን ነገር መገመት አያዳግትም። ግማሹ ንስሃ ይገባል። ከፊሉ ያለቅሳል፣ የቀረው ይዘላል የተተራመሰ ጉባኤ ሆኗል። ይህ ክስተት ሊፈጸም የቻለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የተደረገ የምልጃ ጸሎት ስለነበር ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ዓብይ ተግባር ከሆኑት ነገሮች አንዱ ደግሞ ሰባኪው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንዲኖረው መርዳት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ሰባኪው የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናት ርሃብ በውስጡ እንዲፈጠር በማድረግ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀትና ጠቅላሳ እውቀት እንዲያገኝ ይረዳዋል። *"የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክርና የኃይል መንፈስ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል"* (ኢሳ 11፡2) አ.መ.ት ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ የጥበብና የእውቀት መንፈስ ስለሆነ ለሰባኪው ይህንኑ ያስታጥቀዋል። ብዙ ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ አስተማሪያችን እንደሆነ ያስተምራል *"መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ ሁሉን ያስተምራችኋል"* ዮሐ 14፡26 ይላል። የእግዚአብሔርን ጥልቅ ሚስጥር እና

እውነት ይገልጥልናል (1ኛ ቆሮ 2፡10-13)። ከዚህም ሌላ አንዳንድ ጊዜ አገልጋይን የሚገጥሙት እጣዳፊ ዓይነት ችግሮች ሲገጥሙ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን የመረዳት ብርሃን አለ(ሉቃ 12፡11)። በተዘዋዋሪም መንገድ መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል፣ የማስተማር ሥጦታ ያላቸውን ሰዎች በመጠቀም መንፈሳዊ እውቀት ያስጨብጠናል(1ኛ ቆሮ 12፡28)። ቃሉን የመግለጥ፣ የማብራራት፣ የማብራት፣ የመተርጎም ሥራ እየሠራ መጽሐፍቅዱሳችንን ስናጠና ሙሉ መረዳትን ይሰጠናል።

## 2. የሚያገለግለውን ህዝብ ዓይነት ለይቶ ማወቅ ይኖርበታል

የተሰበሰበው ጉባኤ ምን ዓይነት እንደሆነ፣ ለምን ዓላማ እንደተሰበሰበ ምን ዓይነት መልዕክት እንደሚያስፈልገው ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል። ለምሳሌም ያህል ሐዘን፣ ፋሲካ፣ ሠርግ፣ የልደት ቀን ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሁሉ አንድ ዓይነት መልዕክት ሊኖራቸው አይችልም። የመልዕክቱ ተቀባዮች እነማን ናቸው ብሎ መጠየቅም ሌላው አግባብነት ያለው ገጽታ ነው። የምሰብካቸው ሰዎች። በጣም የተማሩ ናቸው? ያልተማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው? ወጣቶች ናቸው? አረጋዊያን ናቸው? እድሜ እና ጾታ ራሱን የቻለ የአመለካከት አቅጣጫ ሊኖረው ይችላል።

እነዚህን ዝርዝር ሁኔታዎች ጠንቅቀን ማወቃችን ደግሞ ምን ያህል ደቂቃ ለመስበክ እንደምንችል እንድንገምት ይረዳናል። ምናልባት የምናደርገው የንግግር ዓይነት ሊለያይ ስለሚችል ጊዜው እንደዓይነቱ የተለያየ ነው የሚሆነው ጥቂት ምሳሌ ብንወስድ፦

- ስብከት ከሆነ ከ 20-30 ደቂቃ ያህል መሆን ይኖርበታል።
- ትምህርት ነክ ከሆነ ደግሞ ከ 30-40 ደቂቃ ያህል ይወስዳል።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ከ 45-60 ደቂቃ ያክል ሊወስድ ይችላል።

ሰዓቱን ወደዚህን ያህል ደቂቃ መመጠን ያስፈለገው ደግሞ መልዕክት የመያዝ የሰው አቅም ሁኔታ ስለሚለያይ ነው። ሰው በመስማትና በማየት፣ በድርጊት ትምህርት ሊተላለፍለት የአያያዙ ሁኔታ ይለያያል።

- በመስማት 10% ያህል ያስታውሳል፣
- በማየት 30% ያህል ያስታውሳል፣
- በማየትና በመስማት 50% ያህል ሊያስተውል ይችላል፣
- በማየት፣ በመስማትና በማድረግ 70% ያህል ያስታውሳል ያህል የማስታወስ ችሎታ ሊያገኝ ይችላል።

## 3. ስብከትን መጻፍ

ስብከቱን መስበክ ከመጀመር በፊት ሊቀድም የሚገባው ነገር ቢኖር መድረክ ላይ የሚነገረውን ስብከት በጽሑፍ ማስፈር ያስፈልጋል። ስብከትን መጻፍ በጥሩ ሁኔታ በአዕምሮ ለመያዝና በኋላም በሚያምር ሁኔታ ለማቅረብ ይረዳል በስብከት ጊዜ ልንናገር የምናስበውን ሁሉ አሁን ቃል በቃል በጽሁፍ ማስፈር መጀመር አለብን። ይህ ሲባል የፃፍነውን ስብከት ቃል በቃል ሳናዛንፍ እንናገረዋለን ማለት አይደለም መንፈስ ቅዱስ እርሱ በሚፈልገው መልክ ሊነዳን ሐሳቡ ያው ሆኖ በሌላ የቃላት አገላለጽ ልንናገር እንችል ይሆን ይሆናል። በእርግጥ ከዝግጅታችን ጊዜ አንስቶ መንፈስ ቅዱስ በንቃት አብሮን ሲሠራ ቆይቶ መድረክ ላይ ሐሳብህን ለውጥ ይለናል ማለት አይደለም። ምናልባት ግን ለዝግጅታችን እድል ፈንታ ሳንሰጠው ቀርተን ከሆነ በኋላ መድረክ ልንወጣ ስንል የመቃተት ጸሎት ከፍርሃትም ይሁን ከትህትና ስለምናደርግ የሐሳብ ለውጥ እንድናደርግ ሊናገረን ይችላል።

ስብከታችንን በጽሁፍ ማስፈር ከሚሰጣቸው ጥቅሞች መካከል የሚከተሉት ጥቂቶች ናቸው።

- ስብከቱ እንዴት እያደገ እንደሄደ ለማየት የሚረዳና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማጠናከር እንድንችል የሚያግዝ ነው።
- ስብከቱን ሙሉ በሙሉ በምንጽፈው ጊዜ በቀላሉ በአዕምሮአችን ይቀረጻል።

- የጻፍነውን ስብከት ሌላ ጊዜ የተወሰነ ማሻሻያ ወይም እንደ አድማጫችን ሁኔታ አስተካክለን ልንሰብከው እንድንችል ይረዳናል። ካልተጻፈ ግን አይገኝም።
- የስብከቱን ርዝማኔ እና የምንሰብክበትን ጊዜ ለመቆጣጠር ይረዳናል። ምን ያህል ገጽ ብንጽፍ በምን ያህል ደቂቃ እንደምንጨርስ ለማሰብ ይረዳናል።
- የተሻለ ሐሳብ ስናገኝ ስብከታችንን ለመከለስና ለማሻሻል ይረዳናል። ብዙ ሰባኪዎች ስብከታቸውን በጥሩ ዝግጅት ስለማያዘጋጁና የተዘጋጁትንም ስለማይጽፉ የምሳሌ፣ የሐሳብ ድግግሞሽ ያደርጋሉ ይህ ደግሞ አድማጭን ያሰለቻል።

## 3.2 የስብከት አቀራረብ

ለስብከት አቀራረብ የሚጠቅሙ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦

### 1. መንፈስ ቅዱስና የስብከት ዝግጅት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ አንድ ጠቃሚ ጉዳይ ነግሯቸዋል ይኸውም ለአገልግሎት ኃይል መልበስ እንደሚያስፈልጋቸው ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን አግኝተው ኃይል እስኪታጠቁም በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ትዕዛዝን ሰጥቷቸዋል። በሐዋ 1፡1-5 እንዲህ ብሏቸው ነበር *"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* (ሐዋ 1፡8)። ሐዋርያትን ጨምሮ ወደ 120 የሚጠጉ ደቀመዛሙርት ለክርስቶስ ትዕዛዝ በመገዛት ስለተጠባበቁ በጴንጤቆስጤ ቀን ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ሐዋ 2፡1-4 ቀጥሉም በአዲስ መለኮታዊ ብርሃን፣ ቅናት፣ ኃይል እና ስኬታማነት ወንጌልን መስበክ ጀመሩ። በሐዋ 2፡14-40 የተመዘገበውን የጴጥሮስን ስብከት ስናይ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለሰባኪ የሚሠጠውን የተሟላ ስብዕናና ውጤት አጠያያቂ አለመሆን ልብ ልንል እንችላለን። በጴጥሮስ ስብከት ራሳቸውን ለክርስቶስ የሰጠ ሰዎች ቁጥር ሦስት ሺህ ነበር።

የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ሰባኪዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው ያስገኘላቸው ጥቅም ዘርፈ ብዙ ነው። መንፈስ ቅዱስ በመውረዱ ምክንያት አማኞች እንደ ቤተክርስቲያን

ከተዋቀሩበት ጊዜ አንስቶ ሰባኪ ደቀመዛሙርት ያለፉት የመከራ ብዛት ቁጥር አልነበረውም ምክንያቱ ደግሞ ምንም ዓይነት ሀብት፣ ክብር ወይም መከላከያ የሌላቸው መሆኑ ነው። የነበራቸው መሠረታዊ ነገር የእግዚአብሔር ቃል እንደመልዕክት፣ የተለወጠ ማንነታቸው እንደመልዕክተኛ፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንደኃይል ምንጭ ነበር። እስከምድር ጠርዝ ወንጌልን ለማሰራጨት ትልቅ ቅናት፣ የማይዝል ልቦናና ተከታታይነት ያለው ግለት የሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ ነበር።

## 2. ግልጽ በሆነ የቋንቋ አጠቃቀም መስበክ

ስብከት አዘጋጅቶና ጽፎ መጨረስ ብቻውን በቂ አይደለም ያዘጋጀነውን ስብከት ባልተዘበራረቀና ጉራማይሌ ባልሆነ ንፁህ የመስበኪያ ቋንቋችን ማቅረብ መቻል አለብን። አሪስቶትል የተባለ የግሪክ ፈላስፋ *"የምትናገረውን ነገር ማወቅ በቂ አይደለም እንዴት እንደምትናገርም ማወቅ አለብህ"* ብሎ ተናግሯል። በምንናገረው ቋንቋ አማካኝነት ማስተላለፍ ያለብንን መልዕክት ውጤት ሊያመጣ በሚችል መንገድ እንዴት መናገር እንደሚኖርብን የሚያስገነዝብ ነው። ከአሰልቺ አባባሎች በመቆጠብ በጥሩ ድምጽ ጣዕም ባለው መልክና በጥሩ ቃላት፣ የተመጣጠነ ስሜት ባለው ሁኔታ ስብከታችንን ማቅረብ ይኖርብናል። የተጋነነ ከመልዕክቱ ጋር አብሮ የማይሄድ ጊዜን ለመሙላትና አድማጭን ለማዝናናት ሲባል የሚነገር ቀልድ(ጆክ) ስብከቱ የሚያስተላልፈውን ቁም ነገር የሚያጠፋ ነው። ይልቁንም የምናስተላልፈው መልዕክት ፈገግ የሚያሰኝ እንዲሆን አድርገን ልናቀርበው ብንችል ውጤቱ የላቀ ይሆናል። ለዛ ያለውና ታስቦበት የሚነገር ቀልድ መልዕክትን በአድማጭ ውስጥ ለመጨመር ፍቱን መሣሪያ ነው።

## 3. አካላዊ ሁኔታ

ስብከቱን የሚያቀርበው ሰው ፊት፣ አካልና ድምጽ ጋር በእጅጉ የተሳሰረና ወሳኝ ሁኔታ ነው። እነዚህ ሁሉ ቃል አልባ(Non-Verbal) መግባቢያዎች ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ድምጽ አልባ መግባቢያዎች ከንግግር ይልቅ ይበልጥ መልዕክትን የማስተላለፍ አቅም የሚኖራቸው ጊዜ አለ።

# መልመጃ ጥያቄ ሶስት

1. ስብከት ግብዓቶችን ዘርዝር?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------

2. ለስብከት ዝግጅት የሚረዱ ነገሮች ዘርዝር?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------

# ምዕራፍ ስኬታማ ስብከት

## 4.1 የዓይነተኛ ስብከት መለያዎች

ኃይሉ ቸርነት ፕሮፌሰር ሽማለን በርገርን ዋቢ በመጥቀስ የዓይነተኛ ስብከት መለያዎችን በተመለከተ የሚከተሉትን ዝርዝር ሃሳቦች ያቀርባል፡-[1]

1. **የመልዕክቱ ሀሳብ የምስራች ነው።**

- ለብዙዎቻችን ከምስባክ(ፑልፒት) ላይ መቆጣትና መዝለፍ በቀላሉ ሊመጣልን የሚችል ጉዳይ እንደሆነ ብዙ ምስባኮች ይህንን በተግባር ያሳያሉ።
- የምዕራባውያን መድረኮች ግን ሰሚውን በማባበል የበዛ ትኩረታቸውን ሲያደርጉ የኛ ደግሞ በአብዛኛው ቁጣ፣ ዘለፋና ጠንከር ያለ የተግሳጽ ንግግርን ዓይነተኛ መለያው ያደርጋል። ይሁን እንጂ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ሳምንቱን ሙሉ ሲያንገላታው የቆየው አማኝ መጽናናትንና ተስፋን የሚጠብቅባት ብቸኛ ጣቢያ ቤተክርስቲያን መሆኗ ለእኛ ለቃሉ አገልጋዮች ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። እንዲህ ዓይነት እንግልት በበዛበት ህብረተሰብ መካከል የሚኖረው አማኝ የጎደሉት ነገሮች ለፍርሃትና ለበታችነት ስሜት እንደሚያጋልጡት የነገረ ነፍስና የህብረተሰብ ሳይንስ ባለሙያዎች(ተመራማሪዎች) አረጋግጠዋል።
- ስለሆነም ትውልዱ መጽናናትና ድጋፍ የሚሆነው ምርኩዝ የሚያገኘው ለድሆች የምሥራችን ከሰበከው መልካም ነገርን ከተማረና የእርሱን ፈለግ ከተከተለ የምሥራቹ ቃል አብሳሪ ነው። ስለዚህ ትውልዱ ዓይነተኛ ስብከት ለጨለመበት ብርሃንን፣ መንገድ ለጠፋበት ምሪትን፣ ላዘነውም መጽናናትን የሚያቀብል ነው።
- ተስፋ ቆርጦ በእንባ ያለው አማኝ የጌታውን ድምጹን ሰምቶ እንዲነቃ መልዕክቱ ድጋፍን ካቀበለ፣ እንዲሁም አይዞህ ተብሎ በመጽናናቱ የፈረሰ እምነቱ እንዲጠግ የበኩሉን ያዋጣ እንደሆነ፣ ያ መልዕክት ከዓይነተኛ መለያዎቹ አንዱን ይዟል ማለት ነው።

---

[1] ዚኒ ከማሁ

2. **ዓይነተኛ ስብከት ሰባኪው እሱነቱን ገላልጦ የሚያሳይበት የቅንነት ልምዱን የሚያካፍልበት ሁኔታን በተግባር የሚያሳይ ነው።**

- እውነተኛ መልዕክት ተውኔት አይደለም። በተውኔት አርቲስቶች ሌላውን ሆነው መጫወት ከሆነላቸው እጅግ እንደነቃለን። እኛ ግን ስንሰብክ መልዕክት አቀባይ ነን፤ መልዕክቱ ግን ከእኛ እጅግ ይልቃል፡
- ስለሆነም ዓይነታኛ ስብከት ሰባኪው የኖረውን ከማንነቱ እየቀረሰ በተግባር ከራሱ ከፍሎ የሚያሳይበትና ለሚሰሙት ቃሉን ስጋ አልብሶ የሚያቀብልበትን ዕድል ይሰጣል።
- ስብከት ፕሮፓጋንዳ ወይም ስነጽሑፍ ሳይሆን ድርጊት ለበስ የሆነ ከሳባኪው የዕለት ተዕለት ሕይወት የሚፈስ ምዕመናንን የሚያንጽ የአምላክ እርዳታ በሰው ሁኔታ የሚገለጽበት መንገድ ነው።
- ስለዚህ የዓይነተኛ ስብከት ሌላው መለያው መለኮታዊ እውነትን በሰባኪው ሕይወት ውስጥ በተግባር እንድናይ ዕድል የሚሰጥ ክንውን ነው ማለት ይቻላል።

3. **የዓይነተኛ ስብከት ሌላው ገጽታ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ነው።**

- ፑልፒታችን ላይ ስለማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ ተናግረን ስናበቃ የዕለቱ አዋጃችን ቅርጽም ሆነ ይዘት ክርስቶስ እንደ ሞተልን፣ እንደ ተቀበረ፣ እንደ ተነሳ፣ እንዳረገ፣ ተመልሶም እንደሚመጣ ለመናገር ዕድል የማይሰጥ አደረጃጀት ካለው መልዕክታችን ትልቅ ነገር አጉድሎአል።
- የክርስቶስ የማዳን እውነት በየእሁዱ ከፑልፒታችን መጥፋት የሌለበት የሕይውናችን መገለጫ ነው።
- ስለሆነም ውጤታማና ዓይነተኛ ስብከት ምንጊዜም ክርስቶስንና የማዳ ሥራውን ማዕከል ያደርጋል።
- ስብከታችን የዳኑትን ሲያንጽ፣ያልዳኑትን የክርሰቶስን ፍቅር በማስታወቅ ወደዚህ ሕብረት ይጠራቸዋል። ያኔ ግቡን ለሚመታ ዓይነተኛ ስብከት ራሳችንን ሰጠን ማለት ነው።

4. **ዓይነተኛ ስብከት መጽሐፍ ቅዱስን የስልጣኑ ምንጭ ያደረገ ነው።**

- ዛሬ ዛሬ በብዙዎች ዘንድ እየተለመደ የመጣው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ በመልዕክተኛው እጅ ሳይታይ ሰውየው ወየም ሴትየዋ የአድማጮችን ትኩረት የሚስብ ንግግር አድርገው ዕለተ ሰንበት ያበቃል።
- ስብከታችን ግቡን የሚመታው እኛ አሳምረን መናገር ስለምናውቅ ሳይሆን የእውነቱ ባለቤት በሰዎች ልቦና ቃሉ ሲታወጅ ስለሚሠራ ነው።
- ስለሆነም ለቃሉ ታማኝ የሆነ እውነትን በተግባር እውን ለማድረግ መጽሐፉን በአደባባይ ገልጦ ማንበብና ቃሉ እንዲናገር ዕድል መስጠት ቃሉን ለምናውጅ መልዕክተኞች ቀዳሚ ድርጊት መሆኑን በማወቅ ይህንን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለብን።
- መጽሐፍ ቅዱስ የሙታን ደብዳቤ ሳይሆን በገጾቹ ውስጥ የአምላክን ሕያው እንቅስቃሴ በተግባ ገልጦ የሚሳይ አምላክ ክብሩን የገለጠበት መጽሐፍ ነው።
- እንደ አንዳንዶች ልናመልከው ባይቃጣንም በውስጡ ራሱን ሊሰጠን የፈቀደውን አምላክ ለመስማት ሕዝቡ ዕድል እንዲያገኝ ግን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለብን።
- ስለሆነም ሆን ብለን ቃሉን ከየት ክፍል እናዳወጣን በትግባ እያሳየን መልዕክታችንን ማስተላለፍ አለብን።
- ያኔ የዓይነተኛ ስብከት አንዱን ገጽታ ተላበስን ማለት ነው። ስለዚህ ይህንን ተግባራዊ እውነት ተረድተን የምናውጀው መንፈሳዊ አዋጅ ነው።
- ስለሆነም ዓይነተኛ ስብከት የምንናገረውን ሀሳብ ከየት እንዳመጣነው በድምጽም በጣታችንም ክፍሉን እየጠቆምን በማሳየት ለተመልካችና ለአድማጮቻችን ተግባራዊ ዕድል መስጠትን ያካትታል።
- ይህንን ተገንዝበን ዓይነተኛ ስብከት ለሚቀርብበት ለዚህ መንገድ ተጫባጭ ምላሽ እንስጥ።

5. **ዓይነተኛ ስብከት የሕይወት ለውጥን ለማስገኘት የታቀደ ነው።**

- ዓይነተኛ ስብከት ሰዎች መልዕክቱን ከሰሙ በኋላ የሚለውጡትን ነገር በተግባር ለማመልከት ስጋት የሌለበት ነው።

- ስንሰብክ ብዙ መረጃዎችን የምናቀብል ቢሆንም ግባችን ግን እርሱ አይደለም።
- ስለሆም ሰዎች በሙሉ የሚለውጡትን ተግባራዊ ነገር ማየት እንዲችሉ ፍንትው ያለ መረጃን ማቀበል የዓይነተኛ ስብከት መለያ ነው።
- እውነተኛ ስብከት ሰዎች የሚለውጡትን ነገር ያለብዙ ውትወታ እንዲያዩ ይረዳቸዋል።
- ለሕይወት ለውጥ ያልታለመ ስብከት ቅስቀሳ ፕሮፖጋዳ ከመሆን አያልፍም።
- ስለዚህ ስብከት ተግባራዊ ርምጃን በጥቡብ እንዲያሳይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ስብከትም ለሕይወት ለውጥ ታቅዶ ያ በተግባር ሲውል የዓይነተኛ ስብከትን ለዛ ለብሶ ይታያል።

**6. ዓይነተኛ ስብከት ሁሉን ለመድረስ የሚችልና ሁሉንም በእኩልነት የማቀፍ አደረጃጀትን በተግባር እውን ያደረገ ነው።**

- ዓይተኛ ስብከት የአዳማጮችን ማንነትና ምንነት በውል ይገነዘባል።
- በአንድ እሁድ ማለዳ ስብከታችን የሚሰሙ ሰዎች ዓይነታቸው ብዙ ነው።
- በተቻለ መልኩ ሁሉንም መከተት የዓይነተኛ ስብከት መለያ ነው።
- ወጣቶች፣ ባለትዳሮች፣ ላጤዎች፣ ወንዶች፣ ሴቶች፣ ሠራተኞች፣ ሥራአጦች፣ ልጆች፣ አገልጋዮች፣ የእሁድ ደምበኞች እንዲሁም እንግዶች ተሰበጣጥረው ሊያደምጡን ይታደማሉ።
- በዚህ ጊዜ ለአንድ ወገን ያላዳላ መልዕክት ለማስተላለፍ አስተዋይ መሆን ይጠይቃል፤
- ምሳሌዎቻችን አንዱን የሚኮንኑ ሌላውን የሚያጸድቁ መሆን የለባቸውም ፤ በተቻለ መጠን አድሎን የሚያስወግዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል።
- ስብከታችን ሁሉን አቃፊ ሲሆን ተሳክቶልናል ማለት ነው።
- ዓይነተኛ ስብከት ማንም ተንገዋ እንዳቀር ተገቢውን ጥንቃቄ ያደርጋል።
- ወደ ጸሎት ቤት የሚጡትን አዳማጮች በሙሉ መልዕክቱ እንዲደርሳቸው ተገቢውን ጥረት ያደርጋል።

7. **ዓይነተኛ ስብከት ሁሉም በቀላሉ ሊከታተሉት የሚችሉት ነው።**

- ከላይ እንደተገለጸው ወደ ቤተክርስቲያን ብዙ ሰዎች ይመጣሉ። የሚመጡት በሙሉ አማኞች አይደሉም።
- የሚበዙቱ አማንያን መሆናቸው አያጠራጥርም። ስብከት ተሳክቷል የሚባለው ቋንቋው ሁሉን አድማጭ ሊያጠቃልል የቻለ አቀራረብ የተገበረ እንደሆነ ነው።
- የምንናገረው ለረቂቅ ፍጥረታት አይደለም። ስለሆነም የረቀቁ ስነመለኮታዊ ጭብጦችን፣ ጉባኤውን የማይመጥኑ ጥልቀት ያላቸው ሃሳቦችን በማንሳት ዓይነተኛ ስብከት ሰሚዎችን ግራ አያጋባም።
- ስለሆነም ዓይነተኛ ስብከት ብዙውን ጊዜ ብዙኃኑ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ የሚተላለፍ አዋጅ እንደሆነ አረጋግጠን የምንተገብረው እውነት ነው።
- ሰዎች በቀላሉ ሊከታተሉት የቻሉትን ስብከት ያቀረቡ መልዕክተኞች ዓይነተኛውን ስብከት ለማቅረብ ችርነት ተደርጎላቸዋል ማለት ነው።

8. **ዓይነተኛ ስብከት ለሰዎች እውነት የሚቆይበትን ተዛማጅ ምሳሌ በማምጣት የኃይማኖት ምስጢራትን ገላጭ ነው።**

- ሰው በቀላሉ የሚረዳውና በልቡ የሚቀርለት ስብከት ተግባር ለበስ ምሳሌዎችን ማካተት የቻለ እንደሆነ ተገንዝበን በዚህ አኳያም ለስብከታችን ግብ መምታት መጣር ይኖርብናል።
- ይህ ሆነልን ማለት ለዓይነተኛው ስብከት የሚያበቃን አንዱን ነገር በማግኘታችን ተሳካልን ማለት ነው።

9. **ዓይነተኛ ስብከት አጭርና ግልጽ ነው።**

- ስብከታችን ሳያደናግርና ሰሚዎችን ግራ ሳያጋባ ለምንፈልገው ክፍል በቀላሉ ሊደርስ የሚችለው መልዕክታችን ሰሚዎቻችን ሰሚዎቻችን ሊቀርላቸው በሚችል መንገድ የተቀረጸ እንደሆነ ነው።

- የቋንቋ አጠቃቀማችን ጥንቃቄ የተላበሰና ሰሚዎቹን ባሉበት ሁኔታ የሚያገኛቸው ከሆነ ያኔ መልዕክታችን ተቀባዮቹ ጋ ስሚደርስበት መንገድ በውል አጢነናል ማለት ነው።
- ምክንያቱም ማንኛውም ሰው አቀራረባችንን ማራኪና አትኩሮቱን ሙሉ ለሙሉ የሚስበው ሆኖ ካልተገኘ መስማት በሚችለው ሌላው አቅሙ ትኩረቱን ወደ ሳበው ሌላ ጉዳይ ያመራል።
- ስለሆነም ነገራችን አጭርና ግልጽ በማድረግ የሚቀጥለው ምን ይሆን ? በሚል ጉጉት ውስጥ እንዲገኝ መርዳት የዓይነተኛ ስብከት መለያ ነው።
- አጭር ነው ስንል ሊባል በተፈለገው እውነት ዙሪያ ብቻ ያነጣጠረ ነው ማለታችን ነው። ግልጽ ነው ሲባል ደግሞ መንታ ፍቺ በሚሰጡ ቃላት የተሞላ አይደለም ማለታችን እንደሆነ ልብ ይሏል።
- ሰሚዎቻችን እንዲህ ማለቱ ነው፤ አይ እንዲያ ማለቱ ነው በማለት ሳይወዛገቡ በቀላሉ የሚረዱት እውነት ነው ማለት ነው።
- ግልጽነቱ በቀላሉ ወደ ውስጣችን የሚፈስ ጉዳይ አይደለም፤ ይልቁንም በጣም የምንቸገርበት ጉዳይ ነው።
- አማርኛ ቋንቋችን በብዙ ዘይቤአዊ አነጋገሮች የተሞላ በመሆኑ በአንድ አባባል ብዙ መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላልና ነገራችንን አጭር ማድረግ ከባድ ነው።
- ይሁን እንጂ ግልጽ ስብከቶች ከአሻሚና አወዛጋቢ ነገሮች ሆን ብለው በመራቅ ተቀባዮቹ ሊረዱት የታሰበውን ነገር ለተቀባዩ ያደርሳሉ።
- እንግዲህ እኛም ይህንን ተረድተን በቃላት ምርጫና በሀሳብ አደራደራችን ላይ በጥልቀትና በጥንቃቄ በማሰብ፣ ሃሳባችን ተቀባያች ጋ እንዲደርስ የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል።

10. **ዓይነተኛ ስብከት ፍልቅልቅና ደስተኛነትን ለብሰን የምናቀርበው ሲሆን፤ እንዲህ ተጀምሮ እንዲህ ያልቃል በማይባል ሁኔታ ዘወትር በአዲስ ነገር ተሞልቶ የሚፈስ ነው።**

- የምሥራች ነጋሪ የተደበተና የተደበረ ሊሆን አይገባም።

- ስለሆነም ዓይነተኛ ስብከት ዘወትር የሰሚና ትኩረት በሚማርክ አዲስ ነገር የተሞላ ከመሆኑ ባሻገር፣ አቅራቢው ውስጡን ጢም አድርጎ የሞላለትን ደስታ ሌሎች እያዩ እንዲደነቁ፣ እንዲፈነድቁና እንዲጓጉ ዕድል የሚሰጥን ሁኔታ ይፈጥራል።
- ቁጣንና ተግሳጽን ቢያስተላልፍ እንኳን ጨዋነትን በተላበሰ መልኩ ስለሚሆን ዓይነተኛ ስብከት ከመመጻደቅ የጸዳ ነው።
- ስለሆነም ዓይነተኛ ስብከት በሚማርኩ ነገር ከመሞላቱ ባሻገር ለመንፈስ ቅዱስ መገኘት ዕድልን የሚሰጥ ሁኔታ ይፈጥራል።
- ለመንፈስ ቅዱስ ፎርሙላ ማበጀት አይቻልም። ይሁን እንጂ ለሚታዘዙትና የእርሱን እርዳታ ሽተው በጉጉት ለሚጠብቁ መገኘቱን የሚያሳውቁ ልዩ ልዩ ነገሮች በማድረግ ይገኝላቸዋል።
- ስለሆነም ዓይነተኛ ስብከት የኛን መሰጠትና የመንፈስ ቅዱስን ልዩ መገኘት የሚጨምር እንደሆነ ገሐድ ሊሆንልን ይገባል።

## 4.2 የስብከት ተግዳሮቶች

እኛን ሰባኪዎችን የሚሞግተን ባላጋራችን ካለንበት ሁኔታና አድማጮቻችን ካሉበት ሁኔታ ጋር ይተሳሰራል። ከእነዚህም ጥቂቶቹን ኃይሉ ቸርነት እንደሚከተለው ያብራራል፡-[2]

### 1 የስኬት ፈተና

- የብዙ ሰው ፈተና የፈለገውን እንደሚገባ ለማከናወን አለመቻል ነው። ይሁን እንጂ የተሳካላቸው ሰባኪዎች ትልቁ ፈተና መዋረዳቸው ሳይሆን መከበራቸው ነው። ማጣታቸው ሳይሆን ማግኘታቸው ነው። አለመከናወን ሳይሆን ነገሮችን ቀና መሆናቸው ነው። ከሰባኪ አንደበት የሚፈሱ ቃላት በሰው ስሜት ላይ የሚፈጥሩት እንዲህ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ስለሆነም እስከ ዛሬ አያሌ ሰባኪያንን ጠልፈው ከጣሉት ታላላቅ ወጥመዶች የመጀመሪያው መሳካት ይባላል። ሲሳካልን በቃ እኔ እኮ አደረግሁት ማለት ይቃጣናል። በዚያ ጊዜ የልባችንን ንጽሕና የሚነጥቅ እብሪት ይገባብናል።

---

[2] ዚኒ ከማሁ

- መልካም ሥራቸውን ለሰዎች እግዚቢሽን በማቅረብ ከሰዎች ጉገሳ የፈለጉት ፈሪሳውያን በዚህ ፈተና የወደቁ መንፈሳዊ ቡድኖች ነበሩ። ውድቀትና ጉድለት ከጣላቸው ሰባኪዎች መሳካት ጉድ ያደረጋቸው በታሪክ ይበዛሉ።
- ስኬት ትዕቢትን ጎትቶ ውደቀትና መጣል ለሚባሉ ክፉ መልአኮች እንዳይሰጠን ሲሳካልን እንፍራ። እግዚአብሔር የሠራውን የእኛ አድርገን ለመውሰድ ከሚገፋፉን ውስጣዊ ዝንባሌ በመንቃት መቃወም አለብን።
- በመንቀጥቀጥና በመደነቅ ክብሩን ክብር ለሚገባው ጌታ ማምጣት የምንችልበት አቅም እንዲፈጠርልን ጉደዩን ለፈጣሪያችን ያለማቋረጥ በጸሎት እናቅርብ። ብዙ ወገኖችም በጸሎት ሽፋን እንደሰጡን ድጋፋቸውን እንጠይቅ። ያኔ የስኬት ፈተና ጎትቶ ከሚያመጣብን አበሳ እንድናለን ማለት ነው።

## 2 ስብከት ወደ ትወና

- የሰባኪ ሌላው ሞጋች ሁኔታ ሰባኪው የቃሉ አገልጋይ መሆኑን ረስቶት ራሱን አርቲስት ወይም ተዋናይ አድርጎ ማቅረቡ ነው። ተዋናይ ንጉሥ ሳይሆን መሆን ይችላል። ድሃም ሳይሆን ድህነቱን ያውቅበታል። አዋቂም ሳይሆን እንደ አዋቂ መሆን አይጠፋውም። ስለሆነም የወከለውን ገጸ ባህሪ ሆኖ መልዕክቱን ለተመልካች ያቀርባል።
- ይህን በማድረጉ ተዋናይ ሊወቀስ አይችልም። ይልቁንም ወክሎ የተጫወተውን ባህሪ መሆን በመቻሉ በብዙዎች ይሞገሳል።
- ሰባኪ ግን ከተዋናይ ይለያል። በመጀመሪያ ቃሉ እሱን ሊለውጥና በቃሉ ሥልጣን ቁጥጥር ሥር መሆኑን ማረጋገጥና አውን ማድረግ አለበት።
- ያኔ በሕይወቱ ያጣጣመውን ማቅረብ ቀላል ይሆንለታል። አሊያ ግን ነገራችን ወደ ታይታ ይወርድብናል።
- ልብ መባል የሚገባው በዝግጅታችን ወቅት በመጀመሪያ ብርሃን የምንቀበለው የራሳችንን ሕይወት በተመለከተ ነው።

- በስብከት ክንዋኔ ላይ የሚደንቀው ነገር ሌሎችን ልንሰብክ እየተዘጋጀን ለእኛ ግላዊ ኑሮ የሚጠቅም መመሪያ በቀበላችን ነው።
- በሕይወት ፈታኝ ስለሆኑ የሰው ድካሞች ለመስበክ ስንዘጋጅ ኑሮአችንን ፈታሽ የሆኑ ብዙ እውነቶችን እንረዳለን። ለምሳሌ ስለ ስስት፣ ፈተና፣ ራስ ወዳድነት፣ ቅድስና፣ ጸሎት፣ ምስክርነት፣ ትዕግስት፣ ራስን መግዛት፣ ፍቅር፣ ትህትና፣ ትጋት፣ ወዘተ… በመሳሰሉ ርዕሰ ጉዳዮች ለመናገር ስንዘጋጅ ማምለጥ አንችልም። ካመለጥን ግን የቃሉ አገልጋይ መሆን አቁመናል ማለት ነው። ምክንያቱም ከእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ አምልጦ ለመስበክ በመድረክ የሚቆም ሰባኪ ስለ ልዩ ልዩ የመነጽር ሌንሶች መለናገር የቆመ ዓይነ ስውርን፣ ማራኪ ሙዚቃ ለማሰማት አዳማጮች ፊት የቆመን ደንቆሮ ግለሰብን እንዲሁም ፈጣን ሩጫን ለማስተማር በሚዳቋዎች ፊት ከቆመ ኤሊ ጋር ስለሚመሳሰል፣ ድካሙና ጥረቱ ከንቱ ይሆናል።
- ወገኖች ዓይነ ስውሩም ስለ ሌንስ ጠቀሜታ፣ መስማት የተሳነውም ግለሰብ ስላልሰማው ሙዚቃ ድንቅነት እንዲሁም ቀርፋፋው ኤሊ ለፈጣኗ ሚዳቋ ለመናገር ብቃት የላቸውም። ሰባኪው የበቃ እንዲሆን ከፊት ለፊቱ የቆመውን ሞጋች ሁኔታ ማሸነፍ አለበት።

## 3 ወንጌልን መሸቀጥ

- የሰባኪው ሌላ ፈተና ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ሳይሆን የሚፈልጉትን ነገር መናገር ነው። ብዙ ጊዜ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ያዘነባቸው የቃሉ አገልጋዮች(መልዕክተኞች) ጌታ ካለው ይልቅ የሰዎችን ልብ ፍላጎት በማጥናት ለእነርሱ በማጥናት ለእነርሱ የሚስማማውን ብቻ ለማለት በመቁረጣቸው ነው። በእርግጥ ሰዎች ካሉበት ሁኔታ ጋር የሚዛመድ መልዕክት ማቅረብ ይጠበቅብናል። ይህ ሲባል ግን የሳተውን የሚመልስ ተግሳጽ፣ የተሰበረን ልብ የሚጠግን ማጽናኛ፣ አቅጣጫ ለጠፋበት ምሪት፣ ጥበብ ለጎደለው ብርሃንን ተባለ እንጂ ሰዎች የሚፈልጉትን ሁሉ ለማሟላት የሚሆንን ሁኔታ እንፍጠር አልተባልንም።

- ሰባኪን የሚሞግተው የዚህ ዘመን ሁኔታ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ በማስደሰት ላይ የተመረኮዘ አካሄድና አደራረግን መምረጥ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አገልጋይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ለማለት አቅም የለውም። ምክንያቱም እሱን የሚነዳው ሰዎች ምን ይፈልጋሉ የሚለው የሸቀጥ ነጋዴ አስተሳሰብ ነው። ከእግዚአብሔር መልዕክተኛነት ይልቅ በእንዲህ ዓይነቱ ሰው ሕይወት፣ ሱቅ በደረቴነት ያይላል።
- ከሰባኪነት ይልቅ የሽያጭ ክፍል ኃላፊ ቢሆን ይቀለዋል። ስለሆነም እኛም በመሸቀጥ ፈተና ውስጥ እንዳንወድቅ ይህንን ተፋላሚ ሁኔታ ከወዲሁ ተገንዝበን ተገቢውን ርምጃ ልንወስድ ይገባናል።

# 4 የሞት መርዶ ነጋሪነት

- መልካም ነገር ከመናገር ይልቅ ሁልጊዜ በሰው ጉድለትና ሰባራነት ላይ ያነጣጠረ ሰውን በደለኛ የሚያደርግ ማቋረጫ የሌለው ዘለፋን ሰሚን ማጥገብ ሌላው ሰባኪን ከሚሞግት ሁኔታ የሚጠቀስ ነው።
- ቡብሉይ ኪዳን እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች እግዚአብሔር *“ርህራሄ የጎደላቸው በህዝቤ ስቃይ የሚደሰቱ አውሬዎች”* ብሎ በተደጋጋሚ ሲጠራቸው እናያለን።
- ሰውን ያለማቋረጥ በመኮነን ደስታ የሚያገኙ ሰዎች ከስብዕና ተራ ወጥተዋል። ስለሆነም እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ያደረገው ጥሪ ነቢይነትን ከክህነት አቀናጅተው እንዲይዙት መጥራት ነበር።
- የደከመውን እንዲያበረቱ፣ የባዘነውን እንዲፈልጉ፣ የቆሰለውን እንዲፈውሱ፣ የጠገበውን ከተራበው እንዲለዩ ፈለገ። ያኔ ማ ምን እንደሚፈልግ ይለያሉ። ለማን መርዶ ለማን የምሥራች እንደሚያሻ ይገነዘባሉ። እኛም ከዚህ ሞጋች ሁኔታ ራሳችንን አጽድተን «ጸጋና እውነትን ከተሞላው» አዳኛችን ተምረን እውነትን በፍቅር መግለጽ እንጂ ሁልጊዜ የዘለፋ ሰዎች መሆን የለብንም። ምክንያቱም ለማያባራ ዘለፋ ራሳችንን ከሰጠን የሞት መርዶ ነጋሪዎች ወደ መሆን ዝቅ እንላለን ማለት ነው።

- ጌታ ጠንከር ያለ ዘለፋንና ተግሳጽን በበዳዮችና በክፉዎች በተግባር ያደረገ ቢሆንም የእርሱ ወቀሳና ዘለፋ እውነትን በመናገር ላይ ብቻ ሳይሆን የሱ እውነት ለሰዎች ጸጋን ከመስጠት ጋር የተያያዘ ነበር። ለዚህ ነው ጸጋና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ የተባለለት።
- የቱንም ያህል ትልቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ብንሆን ገደብ በሌለው ሁኔታ በሰዎች ላይ ማንባረቅ አልተፈቀደልንም። ዳሩ ግን ከፊት ለፊታችን የተደቀነው አንዱ ሞጋች ሁኔታ መድረኩን በስፋት ስላገኘነው እንድናንባርቅ የሚገፋፋ ነውና ጠንቀቅ ማለቱ ይበጀናል።

## መልመጃ ጥያቄ አራት

1. የዓይነተኛ ስብከት መለያዎችን ዘርዝር?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2. የስብከት ተግዳሮቶችን ዘርዝር?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

# ዋቢ መጽሐፍት


- Moon, K. Jesse, Principles of Preaching, Colombia, Irving, Texas፡ ICI University Press, 1993.
- Batson, George, Expository Preaching Methodolgy for a powerful pulpit, Irving, Texas፡ ICI University Press, 1994.
- Stott, Jon., Between Two Worlds, The Art of preaching in the Twentieth century Grand Rapids, Michigan, Wm. B. Eerdmans publishing Co, 1982.
- Ramm, Bernard, Protestant Biblical interpretation, Revised Edition. Boston፡ W.A Wilde co. 1956.
- ፓስተር ወርቅነህ፣ ተስፋ የመድረክ አገልግሎት (Homiletics) Houston, TX፡ USA, SA.
- Dr. Richard, Ramesh (ገበየሁ አየለ)፣ የገላጭ ስብከት... Addis Ababa, Ethiopia፡ PATON 40-38713 አሳታሚ፣ 1995.
- Braga, James, How to prepare Bible Messages., Portland, Ohegon፡ Multnomah press, 1981.
- Lloyd- jones, D. Martyn. Preaching and Preachers, Grand Rapids, Michigan፡ Zondervan publishing House, 1972.